በመጀመሪያ መኖሪያ ቤት ውስጥ ለመኖር የሚረዳ የሆም አፊስ መመሪያ

## የዚህ መመሪያ ዓላማ

**ይህ መመሪያ በዋነኝነት በመጀመሪያ መኖሪያ ቤት ውስጥ ለሚኖሩ ጥገኝነት ጠያቂዎች የታሰበ ነው፡ ይህም ድጋፍ ለማግኘት ሴክሽን/አንቀጽ 95 ያቀረቡት ጥያቄ እየተገመገመ ሳለ፡ ሴክሽን 95 ድጋፍ ተሰጠዎት ግን ደሞ ወደ ሌላ መኖሪያ ቤት እስኪዛወሩ ወይም እስኪመደቡ ድረስ ወይም በሴክሽን 4 መሰረት ድጋፍ እያገኙ እንደሆነ ነዉ።**

**የሚከተሉትን በጣም አስፈላጊ ነገሮች የያዘ ነዉ:**

- ከእኛ የመኖሪያ ቤት እንዲሁም አገልግሎቶችን ለማግኘት መጠበቅ ይችላሉ።
- ይህንን አገልግሎት የሚሰጡ እና የሚያቀርቡ ተቋማት።
- እኛ ከእርስዎ ምን እንደምንጠብቅ
- ማንኛውም አይነት ችግሮች፡ ስጋቶች እንዲሁም በሁኔታዎ ላይ ያሉትን ለውጦችን በተመለከተ ሪፖርት የሚያደርጉበት ቦታ

**ይህንን የመረጃ መጽሐፍ እንዴት መጠቀም አለብኝ ፧**

ይህንን የመረጃ መጽሐፍ በጥንቃቄ እንዲያነቡ እንመክራለን። ለእርስዎ እና ለቤተሰብዎ አስፈላጊ የሆነውን ማንኛውንም መረጃ እንዲይዙ እንመክራለን። በዚህ የመረጃ መጽሐፍ ውስጥ ብዙ መረጃ አለ፡ ስለዚህ በጣም ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ ላይ እንዲያስቀምጡት እንመክራለን፡ በዚህ መሰረት ወደፊት ይህንን መጽሐፍ ማጣቀስ ይችላሉ።

**ወደ መኖሪያ ቤቱ ስደርስ ምን ይነገረኛል፧**

**ወደ የመጀመሪያው መኖሪያ ቤት ሲደርሱ፡፣ የመኖሪያ ቤት አቅራቢው ስለሚከተሉት ለእርስዎ በጣም አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ይሰጥዎታል፡**

- መኖሪያ ቤት ማቅረብ።
- የግል ደህንነት እንዲሁም ደህና መሆን፡ የአስቸኳይ ጊዜ ወይም የኤመርጀንሲ የጤና እንክብካቤ ያካትታል።
- የመጀመሪያው መኖሪያ ቤት ያለው አቀማመጥ እንዲሁም መደበኛ የዕለት ተዕለት ተግባራት እንዲሁም የሚሰጡ አገልግሎቶችን በተመለከተ።
- ስለ አጠቃላይ መኖሪያ (የሚመለከት ከሆነ) እንዲሁም ስለ መገልገያ መሳሪያዎች፡ መሳለጫዎች እና የተገጠሙ ንብረቶች እንዴት እንደሚሰሩ መረጃ ማግኘት
- የጤና ምርመራ እና ተመሳሳይ አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚያስፈልገው ሂደት ምን እንደሆነ

**በተጨማሪም የሚከተሉትን ያገኛሉ፡:**

- ስለ መኖሪያ ቤት ያቀረበልዎት አካል እና ከእነሱ ምን እንደሚጠብቁ መረጃ።
- ስለ ማይግራንት ሄልፕ እንዲሁም ከእነሱ ምን እንደሚጠበቅ መረጃ እንዲሁም
- መረጃ መጽሐፉ፡ እርስዎ በታላቋ ብሪታንያ ውስጥ በሚኖሩበት ጊዜ ሊያገኟቸው የሚችሏቸውን አገልግሎቶች እንዲሁም የታላቋ ብሪታንያ ባህልን በተመለከተ መረጃን ያጠቃልላል። ይህ ከሌሎች የመኖሪያ ቤት አቅራቢዎን የዚህ ቅጂ እንዲሰጥዎት መጠየቅ ይችላሉ። (URL: https://www.gov.uk/government/publications/asylum-support-uk-rights-

and-expectations) (https://www.gov.uk/government/publications/asylum-support-uk-rights-and-expectations)

**የመግቢያ/የመቀበያ መግለጫ ካልተሰጠዎት ወይም እነዚህ መረጃዎች ካልተሰጡዎት: መኖሪያ ቤቱን ያቀረበው አካል እነዚህን እንዲሰጥዎት ይጠይቁ። ይህ የመረጃ መጽሐፍ በጣም ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ ያስቀምጡት ምክንያቱም በሌላ ጊዜ መልሰው እንዲያነቡት ነው።**

**እባክዎን ያስተውሉ፡** ይህ ሰነድ መመሪያ-ብቻ ሰነድ ነው እና ህጋዊ የታተመ ፖሊሲ የሚተካ አይደለም ወይም ህጋዊ ፖሊሲ ምትክ ሆኖ ጥቅም ላይ እንዲውል አይደለም። ይህ በዋነኝነት ሴክሽን 98 ድጋፍ ለሚቀበሉ እና በሴክሽን 95 ድጋፍ ማመልከቻቸው ላይ ውሳኔ እየጠበቁ ላሉት ነው። ለሴክሽን 95 ስር ድጋፍ ተቀባይነት ላገኙ ግን አሁንም ድረስ ወደ የቢሃላ ሲበተኑ የሚሄዱበት መኖሪያ ቤታቸው ለመመደብ በመጀመርያ መኖርያ ቤት እየጠበቁ ላሉት ነው። በሴክሽን 4(2) አመልካቾች (በኢሚግሬሽን እና ጥገኝነት ሕግ 1999 ሴክሽን 4(2) መሰረት ድጋፍ የሚያገኙ የጥገኝነት ጥያቅያቸዉ ተቀባይነት ያላገኘ ጥገኝነት ጠያቂዎች) የተለየ ዝግጅቶችን በሚሆንበት ሰኣት የሚንጸባረቅ ነዉ።

በመኖሪያ ቤትዎ ወይም በተሰጠው ድጋፍ ላይ ችግር ካጋጠመዎት ወይም የመኖሪያ ቤቱ ፍላጎቶችዎን (ወይም በእንክብካቤዎ ስር ያሉ ሰዎች) እንደማያሟሉ ካሙኑ እና በቂ ካልሆኑ፡ ለምሳሌ በአካል ጉዳተኛነት ምክንያት የሚያስፈልጓቸዉ ነገሮች፡ እነዚህን ጉዳዮችን በተመለከተ ማይግራንት ሄልፐን ያነጋግሩ። የመኖሪያ ቤት ምደባ 'ያለ ምንም ምርጫ' የሚሰጥ ነዉ እናም የግለሰቦችን ደህንነት ለመጠበቅ እና በሚያስፈልገው ነገሮችን ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ነው ፡፡ MH ደግሞ ለሆም ኦፊስ እና ለመኖርያ ቤት ኣቅራቢዎች ጉዳዮን በመመርመር ሙብት እንዲሰጡት ጥያቄ ያቀርባሉ። ማይግራንት ሄልፕ በሚቀጥለዉን መንገድ ማግኘት ይችላሉ:

**ዌብቻት** በሚግራንት ሄልፕ ዌብ ቻት (URL: https://www.timeforstorm.com/CustomChat/MigrantHelp/1/)
በዌብሳይት ላይ ያለዎትን **ጉዳይ ያቅርቡ**: (URL: https://selfserve.migranthelpuk.org/submit-issue/) (https://selfserve.migranthelpuk.org/submit-issue/)
**ነፃ የስልክ የእገዛ መስመር** 0808 8010503.

ስለ መኖርያ ቤትዎ የሚመለከት ጉዳዮች ከ ማይግራንት ሄልፕ ጋር ተገናኝተዉ ኣሳዉቀዉ ነገር ግን እነዚህ የመኖሪያ ቤት ጉዳዮች አሁንም ካልተፈቱ በመኖሪያ ቤት አቅራቢዎች፡ በሆም ኦፊስ በማይግራንት ሄልፕ ላይ ኦፊሴላዊ ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ቁሬታ ካቀረቡ፡ ሆም ኦፊስ ላቀረቡት የጥገኝነት ጥያቄያ ውድቅ ሊያደርገዉ ይችላል ወይም የገንዘብ ድጋፍቸውን ወይም የመኖሪያ ቤታቸውን ድጋፍ ሊያያቋርጠዉ ይችላል የሚል ስጋት ኣላቸዉ። ይህ እውነት አይደለም። ስለ መኖርያ ቤት የምታቀርበዉ ቅሬታ በጥገኝነት ጥያቄዎ ላይ ወይም የመኖሪያ ቤት ድጋፍን ብቁነትዎ ላይ ምንም ተጽዕኖ የለውም።

## ለእኔ ስለ መኖሪያ ቤት እና ስለሚሰጠው ድጋፍ በማቅረብ ሂደት ውስጥ የሚሳተፉ አስፈላጊ ተቋማት እነማን ናቸው፧

**ማይግራንት ሄልፕ** የበጎ አድራጎት ድርጅት ሆኖ ከሆም ኦፊስ ነጻ/ገለልተኛ የሆነ ድርጅት ነው። ማይግራንት ሄልፕ ለእርሶ ምክር ለመስጠት ወይም በእርሶ ጉዳዮች ስለሚቀበሉት ድጋፍ መረጃ መስጠት፡ በመኖርያ ቤትዎ የሚያጋጥም ችግር ሪፖርት ማድረግ ወይም ቅሬታ ማቅረብ፡ ወይም በሁኔታዎ ውስጥ የተከሰተ ማንኛውንም ለውጥ ለሆም ኦፊስ ለማሳወቅ የተመደበ ድርጅት ነዉ። በሚከተሉት መንገዶች ለማይግራንት ሄልፕ ማነጋገር ይችላሉ:

**ዌብቻት** በሚግራንት ሄልፕ ዌብ ቻት [Migrant Help Web Chat](https://www.timeforstorm.com/CustomChat/MigrantHelp/1/) (URL: https://www.timeforstorm.com/CustomChat/MigrantHelp/1/)

በዌብሳይት ላይ ያለዎትን **ጉዳይ ያቅርቡ:** [Raise an Issue - Self Service Portal](https://selfserve.migranthelpuk.org/submit-issue/) (URL: https://selfserve.migranthelpuk.org/submit-issue/)

**ነፃ የስልክ የእገዛ መስመር** 0808 8010503.



**የእርስዎ መኖሪያ ቤት አቅራቢ።** የሆነው የሆም ኦፊስ መኖሪያ ቤት ለማቅረብ የግል ተቋማትን ይጠቀማል። ወደዚህ መኖሪያ ቤት ሲመጡ የሃዉሲንግ ኦፊሰር(የመኖርያ ቤት ኦፊሰር) ይመደብልዎታል፡ ይህ ሰራተኛ ወደ እርስዎ መጥቶ ይቀበልዎታል፡ ወደ መኖሪያ ቤትዎ ያስገባዎታል እንዲሁም ማንኛውንም ጥያቄዎችዎን ይመልስልዎታል።



**የአካባቢ አስተዳደሮች:** ካውንስል ተብለው የሚጠሩት፡ የመንግስት አካል ሆነው በአካባቢው እንደ ትምህርት ቤት እና ሾሻል ሰርቪስ እና የህዝብ መገልገያዎች ያቀርባሉ። በአካባቢው የሚሰጡት አገልግሎቶች እንዲሁም እና አገልግሎቶች ማን እንደሚያቀርብ በሚኖሩበት ቦታ ላይ ይወሰናል።

የእርሶ አካባቢዎን ኮዉንስል ፖስታ ኮድ በመጠቀም በዚህ አድራሻ ማግኘት ይችላሉ: **[Find your local council - GOV.UK (www.gov.uk)](https://www.gov.uk/find-local-council)** በአካባቢዎ የሚገኙ አገልግሎቶችን ዝርዝር መረጃ እንደ ቤተ-መጻሕፍት(ላይብረሪ) እና የድጋፍ ቡድኖች በአካባቢዎ የሚገኝ የካውንስል ዌብሳይት በኩል ማግኘት ይችላሉ።

## በአስቸኳይ ጊዜ የኤመርጀንሲ ግዜ ምን ማድረግ እንዳለብዎት

አስቸኳይ ህክምና የሚያስፈልገው ድንገተኛ የሕክምና አደጋ በሚከሰትበት ጊዜ፡ የወንጀል ሰለባ ከሆኑ ወይም ወንጀል እንደተፈጸመ ከተጠረጠሩ፡ ወይም የእሳት አደጋ ሪፖርት ማድረግ ከፈለጉ፡ ወዲያውኑ 999 በመደወል ለአገልግሎት ኦፕሬተሩ ምን አይነት አገልግሎት እንደሚፈልጉ ይንገሩ – ፋየር (እሳት አደጋ)፡ ፖሊስ ወይም አምቡላንስ ይበሉ። እነዚህን ቁጥሮች በአደጋ ጊዜ ብቻ ነዉ መደወል ያለቦት።

እንግሊዝኛ የማይናገሩ ከሆነ ወደ 999 ሲደውሉ በመጀመሪያ የሚፈልጉትን ቋንቋ መጥራት አለብዎት፡ ከዚያም የቋንቋ አስተርጓሚ ያለ ከሆነ ያቀርብሎታል። ወደ 999 የሚደረግ ደወል ነጻ ነዉ።

**ፖሊስ:** የዓመፅ/በደል ሰለባ ከሆኑ ወይም የአመፅ ስጋት ካለቦት፡ ወይም ወንጀል ሲሰራ ኣይተዉ ከሆኑ፡ 999 በመደወል ፖሊስ ለማነጋገር መጠየቅ አለቦት። አንድ ወንጀል ሪፖርት ማድረግ ከፈለጉ ወይም ወዲያውኑ ምላሽ የማይጠይቅ ወንጀል ሰለባ ከሆኑ ወደ **101** መደወል አለብዎት። ፖሊስ ማግኘት/ መነጋገር በማንኛውም መንገድ የእርስዎን የጥገኝነት ማመልከቻ ላይ ተጽዕኖ እንደማይኖረው ለማረጋገጥ እንፈልጋለን።

**የእሳት አደጋ፡** እሳት ወይም ጭስ የመሳሰሉ ካዩ በመኖርያ ቤትዎ ያሉትን ሰራተኞች ከማሳወቅ በፊት ለአካባቢዎ የእሳት አደጋ ክፍል ሪፖርት ለማድረግ 999 ይደውሉ እና የእሳት ኣደጋ ማንቅያ ደወል ኣላርም ያስነሱት። እሳት ለማጥፋት ወይም ወደ እሳቱ ለመቅረብ መሞከር የለብዎትም፡፡

**አምቡላንስ:** በከባድ ሁኔታ የታመመ ወይም ጉዳት የደረሰዉ ማንኛውም ሰው ካለ እና ሕይወታቸው አደጋ ላይ ከሆነ እና የሕክምና ድንገተኛ ሁኔታ ለ **999** መደወል አለቦት። አንድ አምቡላንስ የማይፈልግ አጠቃላይ የጤና ምክር ለማግኘት **111** መደወል አለብዎት። ይህን ድጋፍ ለማግኘት በመኖሪያ ቤትዎ ላይ ያለ ሠራተኞች ማነጋገር ይችላሉ።

**መገልገያዎች-** ጋዝ ከሸተቶት በቀጥታ ወደ ብሄራዊ የጋዝ መስመር የኤመርጀንሲ ድንገተኛ ግዜ በስልክ ቁጥር **0800 002 001** እንግሊዝ፡ ስኮትላንድ እና ዌልስ ወይም በሰሜን አየርላንድ በ **0800 002 001** ላይ በመጠቀም መደወል አለብዎት፡ ከዚያ ቀጥለዉ ጉዳዩን በቀጥታ ለ ማይግራንት ሄልፕ ሪፖርት ለማድረግ መቻል አለብዎት።

**ጥያቄ ኣለዎት፧**

በመግቢያ መረጃ እንዲሁም በመረጃ መጽሐፍ ውስጥ እዚህ ይመልከቱ
Visit ወይ (http://www.migranthelpuk.org/)

ማይግራንት ሄልፐ በሚከተለው መንገድ ማግኘት ይችላሉ፡

**ዌብቻት** በሚግራንት ሄልፕ ዌብ ቻት (URL:
https://www.timeforstorm.com/CustomChat/MigrantHelp/1/)
በዌብሳይት ላይ ያለዎትን **ጉዳይ ያቅርቡ:** (URL:
https://selfserve.migranthelpuk.org/submit-issue/)
(https://selfserve.migranthelpuk.org/submit-issue/)
**ነፃ የስልክ የእገዛ መስመር** 0808 8010503.

**ይዘት**


| **ክፍል** | **ገጽ** |
|---|---|
| የዚህ መመሪያ ዓላማ | 1 |
| ይህንን የመረጃ መጽሐፍ እንዴት እንደሚጠቀሙ | 2 |
| ወደ መጀመሪያው መኖሪያ ቤት መምጣት | 3 |
| አስፈላጊ ተቋማት | 4 |
| የአደጋ ጊዜ ኤመርጀንሲ | 5 |
| 1. የመኖሪያ ቤት ዓይነቶች እና ጉዞ | 6 |
| 2. ዋና ዋና ተቋማት | 10 |
| 3. ስለ ጉዳዮች ሪፖርት ማድረግ እና ቅሬታ ማቅረብ | 13 |
| 4. የመኖሪያ ቤቶች መለኪያዎች | 16 |
| 5. ገንዘብ እንዲሁም የድጋፍ ክፍያ | 21 |
| 6. ጥያቄዎ ውሳኔ ከተሰጠዉ በኋላ ከዚያ መቀጠል | 24 |
| 7. አስፈላጊ መገናኛዎች | 27 |


## ክፍል 1 የጥገኝነት ጠያቂዎች የመኖሪያ ቤት ዓይነቶች እና ጉዞ

**የጥገኝነት ጥያቄን ለማስኬድ እና ውሳኔ ላይ ለመድረስ የሚወስደው ጊዜ ሊለያይ ይችላል። የእርስዎ ጉዳይ ምን ያህል ውስብስብ እንደሆነ እና ማስረጃዎችን እና ሰነዶችን ለማቅረብ ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ ላይ የተመሰረተ ነው።**

የመኖሪያ ቤት ጨምሮ፡ ለጥገኝነት ጠያቂ የሚሰጥ ድጋፍ ጥገኝነት ጠያቂው እራሱን ለመደገፍ ሌላ አማራጭ በማይኖረው ጊዜ ይሰጣል። የጥገኝነት ጠያቂውን መኖሪያ የመስጠት ሂደት 'ምርጫ የማይፈቀድ' ስለሆነ የት መኖር እንደሚፈልጉ እንዲመርጡ አይፈቅድልዎትም። ሆኖም ግን፡ በአንድ የተወሰነ ቦታ ለመኖር ልዩ ምክንያት ካለዎት፡ ሆም ኦፊስ ይህንን ግምት ውስጥ ያስገባል – የቤቶች ምደባ መመሪያ በዚህ ሊገኝ ይችላል: (https://www.gov.uk/government/publications/asylum-accommodation-requests-policy/allocation-of-asylum-accommodation-policy-accessible) የመኖሪያ ቤት አቅራቢዎ ለእርስዎ የሚሰጠው መኖሪያ ቤት ለእርስዎ የሚያስፈልግዎትን ልዩ ነገር ቤቱን ይህ የሚያሟላ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

ሁለት ዋና ዋና የቤቶች ዓይነቶች አሉ – **የመጀመሪያ የመኖሪያ ቤት (ኢኒሽያል ኣኮሞዴሽን) (ሆቴል ወይም ትላልቅ ጣቢያዎችን ሊያካትት ይችላል) እና የኋላ ከመጀመርያዉ መኖርያ ቤት ስትበተኑ የሚሰጥ የመኖሪያ ቤት (ዲስፐርሳል ኣኮሞዴሽን)**። በሆም ኦፊስ የመኖሪያ ቤት ውስጥ መኖር ግዴታ ኣይደለም፡ ስለሆነም ከቤተሰብ ወይም ከጓደኛ ጋር ለመኖር መምረጥ ይችላሉ። ይህንን አማራጭ ለመውሰድ ከፈለጉ ይህንን ለማይግራንት ሄልፕ ያነጋግሩ ።

- ***የመጀመሪያ መኖሪያ ቤት***

**በአሁኑ ጊዜ የመጀመሪያ መኖሪያ ቤት ውስጥ እየኖሩ ነው፡፡** የመጀመሪያ መኖሪያው ሙሉ የምግብ አገልግሎት፡ ግማሽ የምግብ ኣገልግሎት ወይም ምግብ እራስዎ በማዘጋጀት የሚኖሩበት ቤት ዓይነት ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ በተለምዶ የጋራ መኖሪያ ቤት (ሼሪንግ ኣኮሞዴሽን) የሚባል ሲሆን በሆስቴል ዓይነት ወይም በሆቴል ውስጥም ሊሆን ይችላል፡፡ ግን ደግሞ ሌላ የመኖሪያ ቤት ዓይነት ውስጥ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ሴክሽን 95 የድጋፍ ማመልከቻቸው ላይ ውሳኔ እስኪያገኙ ድረስ ለጥገኝነት ጠያቂዎች ይህ ድጋፍ ካልተሰጦት ወደ ፍጹም ድህነት/ቤት አልባነት የመውደቅ አደጋ ላይ ሊሆኑ ይችላሉ የሚባሉት እና አስቸኳይ የመኖሪያ ቤት የሚያስፈልጋቸዉ የሚሰጥ ነዉ። በተጨማሪም፡ ሴክሽን 95 የድጋፍ ማመልከቻዎች ተቀባይነት ያገኘ (ወይም ሴክሽን 4) የጥገኝነት ጠያቂዎች ሆነዉ የኋላ ለረጅም ግዜ የሚቆዩበት የግዝያዊ መኖርያ ቤት ማረፊያ (የዲስፐርሳል ኣኮሞዴሽን) እንዲዛወሩ የሚጠብቁም የሚሰጥ ነዉ። ከሆም ኦፊስ ድጋፍ ለማግኘት ጥያቄያቸዉ ተቀባይነት ያገኘ የጥገኝነት ጠያቂዎች ቡኋላ ወደ ተለያየ የኋላ መኖርያ ቤት እስኪገኝላቸዉ ድረስ ወይም ያቀረቡት የጥገኝነት ጥያቄ ሙሉ በሙሉ ዉሳኔ እስከሚያገኙ በመጀመርያ መኖርያ ቤት ዉስጥ ሊቆዩ ይችላሉ።

ሰዎች ወደ የኋለኛዉ ከተበተኑ ብኋላ የሚኖሩበት ቤት ከመዛወሩ በፊት በመጀመሪያው የመኖሪያ ቤት ውስጥ የሚቆዩበት ግዜ የተለያዩ የጊዜ ርዝመት ሊኖራቸው ይችላል፡ ግን ደሞ በአሁኑ ግዜ ያለ የመጠበቅ ጊዜ በጣም ረጅም ስለሆነም እርስዎ እስኪዛወሩ ስለሚጠብቁት የጊዜ ርዝመት ምንም መረጃ ልንሰጥዎ አንችልም። በዩኬ ውስጥ ጥገኝነት የሚጠይቁ ሰዎች ቁጥር በጣም ስለ ጨመረ ለሁሉም ሰዉ የሚሆን መኖርያ ቤት ማቅረብ ላይ እጥረት ኣለ፡ ይህ ደሞ ኣስቀድመዉ ወደ ዩኬ ገብተዉ የነበሩ እና በጣም ለረጅም ግዜ መኖርያ ቤት መጠበቅ ላይ ያሉትን ደሞ ተጨማሪ ኣሉ፡ እና ይህ ማለት ደሞ እርሶ ኣሁን ባሉበት የመጀመርያ መኖርያ ቤት ውስጥ ለረጅም ግዜ ሊቆዩ ይችላሉ ማለት ነዉ፡ ሆኖም ግን የመኖርያ ቤት ኣቅራቢዎች እና ሆም ኦፊስ በኣሁኑ ሰኣት ለርሶ የሚያስፈልጎት ነገር መሟላታቸውን ያረጋግጣሉ። የአሁኑ ቤትዎ ፍላጎቶችዎን ካላሟሉ እባክዎን እርዳታ ለማግኘት ማይግራንት ሄልፐን ያነጋግሩ። እነዚህ ፍላጎቶች አሁን ባለው ቤትዎ ውስጥ እንዴት መሟላት እንደማይችሉ ማስረጃ ማቅረብ ኣልቦት ሊባሉ ይችላሉ። ማይግራንት ሄልፕ ችግሩን ለመፍታት ለእርስዎ መኖርያ ቤት ያቀረበሎትን ኣካል ሊጠይቅ ይችላል፡ ወይም በተቻለ ፍጥነት ወደ የኋላ መኖርያ ቤት(ዲስፐርሳል ኣኮሞዴሽን) ሊዛዟሩ ይችሉ እንደሆነ ያጋጠሙዎት ችግር ወደ ሆም ኦፊስ ሊልክ ይችላል።

- ***የኋለኛ መኖርያ ቤት***

ከመጀምርያ መኖርያ ቤት ከተበተኑ ብኋላ የሚኖሩበት የኋላኛዉ መኖሪያ ቤት(ዲስፐርሳል አኮሞዴሽን) ለረጅም ጊዜ የሚቆዩበት ሆኖ ለሆም ኦፊስ ምትክ ሆነው በሚሠሩ የመጠለያ አቅራቢዎች የሚተዳደሩበት መኖሪያ ናቸዉ። የጥገኝነት ማመልከቻዎ ሙሉ በሙሉ እስኪወሰን ድረስ በዚህ የመኖሪያ ቤት ውስጥ ይቆያሉ፡፡ ይህ ማለት ሁልጊዜ በአንድ መኖሪያ ቤት ውስጥ ይቆያሉ ማለት አይደለም።

- **ከቤተሰብ ወይም ከጓደኛ ጋር መኖር (በራስዎ መኖር)**

የጥገኝነት ጠያቂ እንደመሆንዎ መጠን፡ ያቀረቡት የጥገኝነት ጥያቄ ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ በሆም ኦፊስ በመኖሪያ ቤት ውስጥ ከመኖር ይልቅ ከጓደኛዎ ወይም ከቤተሰብዎ ጋር መኖር መምረጥ ይችላሉ። የሚኖሩበት ቦታ በጥገኝነት ጥያቄዎ ውጤት ላይ ተጽዕኖ አያሳድርም።

ብቁ ከሆኑ፡ አስፈላጊ የሆኑ የኑሮ ወጪዎችን ለመሸፈን ድጋፍ ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ ለበለጠ መረጃ፣ እባክዎን የስደተኛ እገዛን ያነጋግሩ።

## የጥገኝነት ጥያቄዉ ውሳኔ ከተሰጠበት በኋላ ወደፊት መቀጠል (ሙቭ ኦን)

**አሉታዊ ውሳኔ**

የጥገኝነት ጥያቄዎ ውድቅ ከሆነ (ይግባኝን ጨምሮ) እና ከእርስዎ ጋር የሚኖሩ ልጆች ከሌለዎት፡ ለሌላ የተለየ የሆም ኦፊስ ድጋፍ እስካላመለከቱ ድረስ ከመኖሪያ ቤቱ መውጣት አለብዎት። የጥገኝነት ጥያቄዎ ውድቅ ከሆነ እና ከእርስዎ ጋር የሚኖሩ ልጆች ካሉዎት የጥገኝነት ድጋፍ ይቀጥላል። የጥገኝነት ጥያቄዎ ውድቅ ከሆን እና ጊዜያዊ እንቅፋቶች ከሌሉ፡ ከዩኬ እንዲወጡ ይጠበቃሉ። ዉሳኔዉ ከሆም ኦፊስ ከተሰጦት በኋላ በአጭር ግዜ ማይግራንት ሄልፕ ምክር እና መመርያ ይሰጦታል። ስለዚህ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፡ በበጎ ፍቃድ የመመለስ ኣገልግሎት ከሰኞ ጥዋት 9 ሰኣት እስከ 5 ሰኣት ከሰኣት በስልክ ቁጥር 0300 004 0202 ኣገልግሎት ይሰጣል። (https://www.gov.uk/return-home-voluntarily)

**አዎንታዊ ውሳኔ**

ለሊቭ ቱ ሪሜይን የመኖሪያ ፈቃድ ከተሰጣችሁ እርስዎ እና የቤተሰብዎ አባላት ከ የጥገኝነት ጠያቂዎች መኖሪያ ቤት ለቀው መውጣት አለብዎት፡ እና የሆም ኦፊስ ድጋፍ ደሞ የሚቆም ይሆናል። የሊቭ ቱ ሪሜይን የመኖሪያ ፈቃድ ከተሰጣችሁ፡ ስራ እንዲሰሩ ተፈቅዶልዎታል፡ ለሕዝብ ድጋፍ(ፓብሊክ ሰርቪስ) ብቁ ነዎት፡ ቤት መፈለግ እና በዩኬ ውስጥ እንደ ማነኛዉ ነዋሪ ተመሳሳይ ድጋፍ የማግኘት መብት አለዎት። ልብ ይበሉ፡ በዩኬ ውስጥ የመኖርያ ቤት እጥረት ኣለ ስለዚህም የራስዎን ቤት ለመከራየት ግዜ ሊፈጅቦት ይችላል። ምንም እንኳን የኣከባቢዉ ኣስተዳደር ምክር እና መረጃ የሚሰጦት ቢሆንም የራስዎ የግል መኖርያ ቤት መፈለግ ሊያስፈልጎት ይችላል። ከማይግራንት ሄልፕ ጋር የሚደረግ የ ሙቭ ኦን ስልክ ጥሪ ምክር እና መመርያ ይሰጦታል፡ ይህ ደሞ ዉሳኔዉ ከተወሰነ በኋላ በ24 ሰኣት ዉስጥ የሚሰጥ ይሆናል፡ ወይም የኣከባቢዉ ኣስተዳደር ጋር በመደወል ይህንን መረጃ ማግኘት ይችላሉ።

## የሚጠበቁ ነገሮች

ሁልጊዜ በአክብሮት፡ በፍትሃዊነት እና ያለምንም አድልዎ የሌለዉ መንገር ነዉ የሚያስተናግዱ። በተመሳሳይ መልኩ እርስዎ ሁሉንም ሰራተኞች እና ከእርስዎ ጋር የሚኖሩ ሰዎችን በተመሳሳይ መንገድ መያዝ አለብዎት። የመኖሪያ ቤትዎን በተመለከተ ማንኛውም ችግር ካለ፡ ችግሩን እንዳዩ ወዲያውኑ ለማይግራንት ሄልፕ ሪፖርት ማድረግ አለብዎት። **የጥገኝነት ማመልከቻዎን ወይም የጥገኝነት ድጋፍ የማግኘት መብትዎ ላይ ሪፖርት በማድረግዎ ምንም ዓይነት ችግር አይደርስብዎትም።**

## ሚስጥራዊነት እና መረጃ ማጋራት

የሆም ኦፊስ እና አቅራቢዎቻችን የእርስዎን የግል መረጃ በሚስጥር ይይዛሉ እና ይጠብቃሉ። ነገር ግን መረጃዎን ለሌሎች ኤጀንሲዎች የምናጋራባቸው አንዳንድ ሁኔታዎች አሉ። እነዚህም የሚከተሉትን ያካትታሉ፡

- ከአካባቢያዊ ካውንስል ጋር መረጃ መጋራት ይህም ማለት ለሾሻል ኬር፡ የመኖሪያ ቤት ስፔሻሊስት፡ ወይም የመኖሪያ ቤት ማሻሻያዎች ለእርስዎ እንዲደረግ ነው።
- ከጤና አገልግሎት ጋር መረጃ ማጋራት ይህም እርስዎ ያለብዎትን አጠቃላይ የጤና ፍላጎቶች እና ማንኛውንም የጤና ችግሮች በተመለከተ ተገቢውን የጤና እንክብካቤ እያገኙ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው።
- እርስዎን እና ቤተሰብዎን በተለይም ልጆችን እና ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ሰዎችን ለመጠበቅ መረጃ ማጋራት።
- አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ አስፈላጊ መረጃዎችን ለትምህርት ባለስልጣን ማጋራት።
- በዚህ ማህበረሰብ ውስጥ ደህንነትዎን ለመጠበቅ እንድንችል ወንጀልን በተመለከተ ለፖሊስ ሪፖርት ማድረግ።
- ማጭበርበርን ለመከላከል መረጃ ማጋራት
- ከፍርድ ቤት ሂደት ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ማሳወቅ

ማንኛውም የእርስዎን መረጃ የተቀበለ ኤጀንሲ የእርስዎን የግል መረጃ ሚስጥራዊነት መጠበቅ አለበት። ለሆም ኦፊስ ወይም ለሌሎች ተቋማት ስለእርስዎ ያላቸውን መረጃ ለማየት በርዕሰ ጉዳይ የመመልከት ጥያቄ/ሳብጀክር አክሰስ ሪከየስት ጥያቄ “subject access request” ማቅረብ ይችላሉ። (https://www.gov.uk/government/publications/personal-information-use-in-borders-immigration-and-citizenship/borders-immigration-and-citizenship-privacy-information-notice)

## የድጋፍ ቅድመ ሁኔታ

- **ለእርስዎ የተደረጉትን የጉዞ ዝግጅቶች መከተል አለብዎት።** ለምሳሌ ወደ ሌላ መኖሪያ ቤት መሄድ። የጉዞ ዝግጅቶችን ለመከተል የማይችሉበት ምክንያት ካለዎት በቅድሚያ ለሆም ኦፊስ ማሳወቅ አለብዎት።
- **እርስዎ ለመኖር በተፈቀደልዎ አድራሻ መኖር አለብዎት።** ከቦታው ከ7 ቀናት በላይ ወደ ሌላ ቦታ መሄድ ከፈለጉ፡ ከሚግራንት ሄልፐ ጋር በመገናኘት ከሆም ኦፊስ ፈቃድ ማግኘት ያስፈልግዎታል። በማንኛውም የ6 ወራት ጊዜ ውስጥ ከ14 ቀናት ወይም ሌሊቶች በላይ ከቤቱ ሳይገኙ መቅረት አይፈቀድልዎትም።
- **የሚኖሩበትን መኖሪያ ቤት ህጎች መከተል አለብዎት።** የመኖሪያ ቤት አቅራቢው የመኖሪያ ቤቱን ህጎች ይነግርዎታል።
- **የጥቃት ባህሪ ማሳየት የለብዎትም ወይም የቃል ወይም የአካል ጥቃት ማድረስ የለብዎትም እንዲሁም የታላቁ ብሪታንያ ህጎችን መከተል አለብዎት።** የጥቃት ባህሪያትን ማሳየት በወንጀል ሊያስከስስዎት ይችላል እንዲሁም የመኖሪያ ቤትን እና የገንዘብ ድጋፍ የማጣት አደጋ ሊያስከትል ይችላል።
- **የሚሰጥዎት የገንዘብ ድጋፍ በመደበኛነት መውሰድ አለብዎት፡** የሴክሽን 95/ሴክሽን 4 ድጋፍ ተቀባይነት ሲያገኝ፡ በመጀመሪያው መኖሪያ ቤት ውስጥ በሚኖሩበት ጊዜ ማንኛውንም ተጨማሪ ወጪዎች ለመሸፈን ሳምንታዊ የገንዘብ ድጋፍ ይሰጥዎታል።
- **የሆም ኦፊስ ጥያቄዎችን መመለስ መቻል አለብዎት።** እነዚህ ጥያቄዎች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፡
    - ከጥገኝነት ጥያቄዎ ጋር የተያያዘ መረጃ።
    - ከጥገኝነት ጠያቂዎች የሚሰጥ ድጋፍ ጋር የተያያዘ መረጃ እንዲሁም
    - በማንኛውም ቃለ መጠይቅ ላይ መገኘት መቻል አለቦት

የተሰጠዎትን ድጋፍ ቅድመ ሁኔታ ካላሟሉ ድጋፍን የማጣት አደጋ አለብዎት።

## በሁኔታዎ ላይ ያለ ኣዲስ ለውጥ

**ጥገኝነት መጠለያ እና ድጋፍ በሚቀበሉበት ጊዜ በሁኔታዎ ውስጥ ማነኛዉ ኣይነት ለውጦች ካሉ ወዲያውኑ ለሆም ኦፊስ ማሳወቅ አለብዎት።** ይህንን ለማድረግ ቀላሉ መንገድ በማይግራንት ሄልፐ በኩል ነው። ከአሁን በኋላ

መኖሪያ የማያስፈልጎት ከሆነ አሁንም በዚህ ሁኔታ ላይ ሆነዉ የገንዘብ ድጋፍ ማግኘት ይችላሉ። ግን በመጀመሪያ ማመልከት አለብዎት (ሆኖም ግን ይህ በሴክሽን 4 ስር ድጋፍ ለተሰጣቸው ሰዎች እውነት አይደለም) ።

**ለሆም ኦፊስ ማሳወቅ ያለብዎት የሁኔታዎ ለውጦች የሚከተሉት ናቸው:**

- ገንዘብ ወይም ፋይናንስያዊ ንብረት ካገኙ ወይም ማግኘት ከቻሉ
- ስኮላርሺፕ ወይም ሌላ ማንኛውም የትምህርት ሽልማት ካገኙ
- ስራ ካገኙ (ስራ ከማግኘት በፊት መስራት የሚፈቀድልዎት ከሆነ ማረጋገጥ አለብዎት - (https://www.gov.uk/government/publications/handling-applications-for-permission-to-take-employment-instruction/permission-to-work-and-volunteering-for-asylum-seekers-accessible)
- የመኖሪያ ቤት አቅራቢዎች ሳያውቁ ወደ ሌላ አድራሻ ከተዛወሩ፡ ወይም ከቤተሰብዎ፡ ከጓደኞችዎ ወይም ከትዳር ጓደኛዎ ጋር ለመኖር ከወሰኑ።
- ከተጋቡ፡ ከተፋቱ፡ ከተለያዩ ወይም ሲቪልያዊ ትስስር ካደረጉ
- ሆስፒታል ከገቡ ወይም እስር ቤት ከገቡ
- እርስዎ (ወይም የትዳር ጓደኛዎ) እርጉዝ ከሆኑ ወይም ልጅ ከወለዱ
- ማንኛውም ልጅዎ ከትምህርት ቤት ወይም ከቤት ከወጣ
- ሌላ የቤተሰብ አባል ወደ ዩኬ መጥቶ እርሶን ከተቀላቀለ ወይም ከዩኬ ከወጣ
- ሌላ ሰው ወደ ቤተሰብዎ ከተቀላቀለ ወይም ከወጣ
- ስምዎን ከቀየሩ
- ከዩኬ ወጥተው ወደ ሀገርዎ ለመመለስ ካቀዱ

**ስለ ሁኔታዎ የተከሰተ ለውጥ ካልነገሩን፡ የሚከተሉት ሊከሰቱ ይችላሉ:**

- ከሆም ኦፊስ የሚያገኙት ድጋፍ ሊቋረጥ ይችላል
- ሊያገኙት የሚገባዎትን ተጨማሪ ድጋፍ አለማግኘት (እንደ የእርግዝና እና የወሊድ ክፍያ ያሉ)
- ሊሰጥዎት የማይገባቸዎትን የተሰጦትን ያልተገባ ድጋፍ መመለስ
- በኢሚግሬሽን እና ጥገኝነት ህግ 1999 መሰረት በተፈጸመ ወንጀል ወንጀለኛ መሆን

## የጥገኝነት ጠያቂዎች የሚሰጥ ድጋፍ ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማለት

**ብዙውን ጊዜ የሚከተሉት ነገሮች ከተከሰቱ ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት (የጥገኝነት ድጋፍ) ይግባኝ ማለት ይችላሉ፡**

- የጥገኝነት ድጋፍ እና/ወይም የመኖሪያ ቤት ጥያቄዎ ውድቅ ከተደረገ
- በሴክሽን 4 መሰረት የጥገኝነት ድጋፍ እያገኙ የነበረ ሲሆን ነገር ግን አሁን ከተቋረጠ።
- በሴክሽን 95 መሰረት የጥገኝነት ድጋፍ እያገኙ የነበረ ሲሆኑ እና ድጋፉ በሌላ መንገድ ካልተጠናቀቀ ከተቋረጠ።.

ማመልከቻዎ ውድቅ ከተደረገ ወይም የሚሰጦት ድጋፍ ከተቋረጠ፡ ውሳኔው ለምን እንደተደረገ የሚያብራራ ከሆም ኦፊስ ደብዳቤ ያገኛሉ። ደብዳቤው ይግባኝ መጠየቅ ይችሉ እንደሆነ እና እንዴት ይግባኝ መጠየቅ እንደሚችሉ ያሳውቅዎታል። ፍርድ ቤቱ ከመንግስት ገለልተኛ ነው። ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ከማድረጉ በፊት የችሎቱ ሁለቱንም ወገኖች ይሰማል። የሚሰጦትን ድጋፍ ተቋርጦ ከሆነ እና በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ ጠይቀዉ ከሆነ፡ ይህ ይግባኝ ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ ብዙውን ጊዜ ድጋፍ ማግኘት ይቀጥላሉ። የይግባኝ ቅጽ እዚህ ማግኘት ይችላሉ (https://www.gov.uk/appeal-first-tier-asylum-support-tribunal)

**ይግባኝ ከማቅረብዎ በፊት እርዳታ እና ምክር ማግኘት ይችላሉ፡**

- የይግባኝ ቅጹን ወደ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት (የጥገኝነት ጠያቂ ድጋፍ) ከላኩ፡ ነጻ የህግ ውክልና ለማግኘት የጥገኝነት ጠያቂ ድጋፍ የይግባኝ ፕሮጀክት (አሳይለም ሳፖርት አፒል ፕሮጀክት ኤኤስኤፒ) ማግኘት ይችላሉ። (http://www.asaproject.org/)
- ምክር እና ድጋፍ ለማግኘት የረፊጂ ኣክሽን (በኢንግላንድ ውስጥ በተለያዩ ክልሎች ውስጥ የሚሰራ) እና ረፊጂ ካዉንስል (በኢንግላንድ እና ዌልስ) ማግኘት ይችላሉ - እነዚህ ሌላ የሚረዳዎትን ድርጅት ሊያገኙልዎት ይችላሉ። (https://www.refugee-action.org.uk/our-services/increasing-justice-tackling-poverty/) (http://www.refugeecouncil.org.uk/)
- ጠበቃ ጨምሮ ሌላ ህጋዊ ምክር ማግኘት ይችላሉ። ለበለጠ መረጃ (http://www.gov.uk/find-a-legal-adviser) ይጎብኙ።
- ተጨማሪ መረጃ በ (http://www.gov.uk/appeal-first-tier-asylum-support-tribunal) ማግኘት ይችላሉ

## ክፍል 2 አስፈላጊ ተቋማት

### ሆም ኦፊስ

**ሆም ኦፊስ ምንድን ነዉ፧**
የሆም ኦፊስ በታላቋ ብሪታንያ ደህንነት እና ኢኮኖሚ ውስጥ መሰረታዊ ሚና አለው። የሆም ኦፊስ የኢሚግሬሽን እና የፓስፖርት ጉዳዮችን፡ የኣደንዛዥ እጽ ፖሊሲን፡ ወንጀልን፡ የእሳት አደጋን፡ ፀረ-ሽብርተኝነትን እና ፖሊስን የሚመራ የመንግስት ክፍል ነው። በቀጥታ ሊያነጋግሩት የሚችሉት የሆም ኦፊስ ክፍል የጥገኝነት እና ጥበቃ ጉዳዮች ይባላል።.

**ከሆም ኦፊስ ምን መጠበቅ እችላለሁ፧**
የጥገኝነት ማመልከቻዎ በጥገኝነት ቡድን የደንበኞች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት(ካስተመር ሰርቪስ ዳይሬክተሮት ኣሳይለም ኦፕሬሽን ቲም) ይታያል እና ይገመግማል። ይህ የሆም ኦፊስ ክፍል ነው። የጥገኝነት ማመልከቻዎ ስኬታማ መሆኑን እና አለመሆኑን(አዎንታዊ ውሳኔ የሚሰጠዉ ነዉ ወይ) መወሰን በእነሱ ገምጋም ነዉ የሚወሰነዉ፡ እና ስለሚወሰነው ውሳኔ እርሶን ያገኝዎታል።

በሆሞ ኦፊስ ውስጥ የጥገኝነት ጠያቂ ድጋፍ ቡድኖች እርሶ ምን ዓይነት ድጋፍ እንደሚያገኙ የመወሰን እና ይህንን ድጋፍ የሚሰጡትን የአገልግሎት አቅራቢዎች የመከታተልን ሃላፊነት አለባቸው። የጥገኝነት ጠያቂዎች ድጋፍ ቡድኖችም በዚህ የመረጃ መጽሐፍ ውስጥ የተገለጹትን የመኖርያ ቤት ኣቅራቢዎች ማሟላት ያለባቸዉን ነገሮች እንደሚያሟሉ ያረጋግጣሉ።

**የሆም ኦፊስ ከእኔ ምን ይጠብቃል፧**
የሆም ኦፊስ የሚሰጥዎትን ድጋፍ ሁሉ ቅድመ ሁኔታዎች እንዲያሟሉ እና በሁኔታዎ ላይ የሚከሰት ማንኛውንም ለውጥ እንዲያሳውቁ ይጠብቃሉ። ይህንን ካላደረጉ፡ ቀጣይ የድጋፍ መብትዎ ሊጎዳ ይችላል።

ከሆም ኦፊስ የሚደርሱዎትን ደብዳቤዎች ችላ አይበሏቸው፡ ምክንያቱም ይህ የሚሰጥዎትን ድጋፍ ሊያቋርጥ ወይም ዉድቅ ሊደረግ ይችላል። ደብዳቤው ምን ማለት እንደሆነ እርግጠኛ ካልሆኑ፡ ምክር እና መመሪያ ለማግኘት ማይግራንት ሄልፐን ያነጋግሩ።

በመንግስት ስለሚሰጡ አገልግሎቶች ተጨማሪ መረጃ በሚከተለው ማግኘት ይችላሉ (http://www.gov.uk/)

### የእርስዎ የመኖሪያ ቤት አቅራቢ

**የመኖሪያ ቤት አቅራቢ ማለት ምንድን ነው፧**
የመኖሪያ ቤት አቅራቢ ለጥገኝነት ጠያቂዎች መኖሪያ ቤት ለማቅረብ እና መኖሪያ ቤቱን ለማስተዳደር በሆም ኦፊስ ኮንትራት የተሰጠ ተቋም ነው። የመኖሪያ ቤት አቅራቢዎች እንደ አካባቢያቸው ይለያያሉ።




**ከላይ ያለው ስዕል ትርጉም**
ስኮትላንድ፡ ሚርስ ግሩፕ
ኖርዘርን አየርላንድ፡ ሚርስ ግሩፕ
ኖርዝኢስት፡ ዮርክሻየርን ሃምበርሳይድ፡ ሚርስ ግሩፕ
ኖርዝዌስት፡ ሴርኮ
ሚድላንድ እና ኢስት ኢንግላንድ፡ ሴርኮ
ዌልስ፡ ክሊርስፕሪንግ ሬዲ ሆምስ
ሳውዝ፡ ክሊርስፕሪንግ ሬዲ ሆምስ እና ሲቲኤም (ሆቴል ብቻ)

**ከመኖሪያ ቤት አቅራቢው ምን መጠበቅ አለብኝ፧**

- የመኖሪያ ቤት አቅራቢው የሚሰጠው አገልግሎት የሚከተሉትን ያካትታል፡
- ንጹህ፡ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ለመኖር የሚያስችል መኖሪያ ቤት፡ የቤት እቃዎች፡ መሳሪያዎች እና አገልግሎቶች ያሉት የመኖሪያ ቤት ማቅረብ እና ማስተዳደር
- መጀመሪያ በመጡበት ጊዜ ስለሚሰጡዎት አገልግሎቶች የሚያካትት ስለ መኖሪያ ቤቱ መግቢያ መረጃ መስጠት።
- ምግብ ያለው መኖሪያ ቤቶች፡ በቀን ሦስት ጊዜ የምግብ አቅርቦት አገልግሎት እና አስፈላጊ የግል ንፅህና እቃዎችን እና የሽንት ቤት እቃዎችን ማቅረብ።

እንደ አማራጭ ደግሞ ለራሳቸው ምግብ እያዘጋጁ የሚመገቡበት የመኖሪያ ቤቶች ውስጥ ያሉ ሰዎች፡ እነዚህን ፍላጎቶች ለማሟላት የሚያስችል ወጪን ለመሸፈን ገንዘብ መስጠት። *ልብ ይበሉ፡ በሴክሽን 4 ድጋፍ ውስጥ ያሉ ሰዎች የገንዘብ ድጋፍ የማግኘት መብት የላቸውም፡ አስፈላጊ ከሆነ ደግሞ ወደ አስፐን ካርድ የሚገባ ገንዘብ ይሰጣቸዋል)።*

- ነፍሰ ጡር ሴቶች እና ሕፃናት ሙሉ የምግብ አቅርቦት ወይም የግማሽ የምግብ አቅርቦት በሚሰጥበት መኖርያ ቤት ተጨማሪ የምግብ እና የኑሮ አስፈላጊ ነገሮችን ለማሟላት ተጨማሪ አቅርቦት (ናፒስ፡ ፎርሙላ፡ ወተት፡ የምግብ አቅርቦት መጨመር፡ የህጻናት ማጠጫ ጥጦ ማጽጃ መሳሪያዎች ወዘተ) የማግኘት መብት አላቸው።.
- ጥሩ ህይወትን ማስቻል፡ ይህም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለሚመለከታቸው ኤጀንሲዎች ሪፈራል ማድረግን ያካትታል።
- ከእርስዎ ጋር በሚነጋገሩበት ጊዜ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ የንግግር እና የጽሑፍ ትርጉም አገልግሎት መስጠት
- የአስተያየት እና የቅሬታ ሂደት መግለጽ እና ማንኛውም አቤቱታ በሚቀርብበት ጊዜ በ 5 የስራ ቀናት ውስጥ መፍታት።
- በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ ፀረ-ማህበራዊ ወይም አስቸጋሪ ባህሪያትን መቆጣጠር።
- በአቅራቢያዎ ያለውን የአጠቃላይ ሐኪም (ጂፒ) የት እንዳለ ማሳወቅ ወይም ከዚህ በፊት የጤና ችግር ካለብዎት በአጠቃላይ ሐኪም እንዲመዘገቡ መርዳት (በቦታው ላይ የነርስ ፕራክቲሽነር ሐኪም ከሌለ)
- መጀመሪያ በመጡበት ጊዜ፡ ወይም በመኖሪያ ቤት ውስጥ በሚኖሩበት ጊዜ፡ የጤና እንክብካቤ ካስፈለጎት እንዲያገኙ መርዳት (ይህ በነዋሪዎች ደህንነት አስተዳዳሪዎች፡ በደህንነት ቡድኖች፡ ወይም በቤት አስተዳዳሪዎች በኩል ሊከናወን ይችላል)
- ለሴክሽን 4 እና ሴክሽን 98 ድጋፍ ብቁ ለሆኑ ሰዎች የጉዞ እገዛን ማቅረብ - ትራንስፖርት ማዘጋጀት ወይም የህዝብ ትራንስፖርት ትኬት በማቅረብ - ለህክምና፡ ለጥርስ ህክምና እና ለሆስፒታል ቀጠሮዎች፡ ለቅድመ ወሊድ ወይም ከወሊድ በኋላ የሚደረግ ቀጠሮዎች፡ ወይም የቤተሰብ አባል ልደት ወይም ሞት ለመመዝገብ ለመጓዝ። እባክዎን ልብ ይበሉ፡ አከባቢዎ ላይ የሚገኙ የጤና እና የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎቶችን በተቻለ መጠን መጠቀም ኣለባቸዉ፡ *እና ለማንኛውም ቀጠሮ ማረጋገጫ ማቅረብ እንዳለብዎ ልብ ይበሉ (ለምሳሌ የቀጠሮ ደብዳቤ) እና ይህንን አገልግሎት ለኣገልግሎት አቅራቢ በተቻለ ፍጥነት ማሳወቅ አለብዎት። ይህ ደሞ በሚመቸዉ ግዜ ይህንን ለማዘጋጀት እንዲችል ነዉ። ማነኛዉን ስለ ጉዞ የተመለከተ ጉዳይ ካለዎት ወደ ማይግራንት ሄልፕ እንድታዋሩ እንማጸናለን።*

በመጀመሪያ መኖሪያ ቤትዎ ውስጥ በሚኖሩበት ጊዜ በመኖሪያ ቤትዎ ውስጥ ችግር ካጋጠምዎት በሚከተሉት መንገዶች ለማይግራንት ሄልፕ ማሳወቅ አለብዎት፡

**ዌብቻት በሚግራንት ሄልፕ ዌብ ቻት (**URL: https://www.timeforstorm.com/CustomChat/MigrantHelp/1/)
**በዌብሳይት ላይ ያለዎትን ጉዳይ ያቅርቡ፡ (**URL: https://selfserve.migranthelpuk.org/submit-issue/) (https://selfserve.migranthelpuk.org/submit-issue/)
**ነፃ የስልክ የእገዛ መስመር 0808 8010503.**

ከዚያ በኋላ እነሱ በእርስዎ ምትክ ጉዳዩን ለመኖሪያ ቤት አቅራቢዎ ያቀርባሉ። ለበለጠ መረጃ 'ስለ ጉዳዩ ሪፖርት ማድረግ እና ቅሬታዎች' ይመልከቱ።

የሆም ኦፊስ መንበሪ ቤት የግድ እዛ መኖር ኣለብክ ማለት ኣይደለም፡ የጥገኝነት ጥያቄዎ ዉሳኔ እስከሚሰጠዉ ድረስ ከዘመድ ወይም ከቤተሰብ አባል ጋር ለመኖር መምረጥ ይችላሉ። እርሶ እየኖሩበት ያሉትን የመኖሪያ ቦታ የጥገኝነት ማመልከቻዎን ውጤት አይጎዳውም። ስለ እራስዎን ችለዉ መኖር የበለጠ መረጃ በኣሳይለም ሳፖርት፡ ከዘመድ ወይም ከቤተሰብ ሊገኝ ይችላል

**የመኖሪያ ቤት አቅራቢው ከእኔ ምን ይጠብቃል፤**
መኖሪያ ቤቱን በአግባቡ መያዝ አለብዎት። ይህም ንጽህናን መጠበቅን እና በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ ያሉትን መሳሪያዎች እና ንብረቶች እንዳይበላሹ መጠንቀቅን ያካትታል።
እንዲሁም ከእርስዎ ጋር በመኖሪያ ቤት ውስጥ የሚኖሩትን ማንኛውንም ሰው እና የሚያገኟቸውን ማንኛውንም ሰራተኞች በአክብሮት ማስተናገድ አለብዎት።

## ማይግራንት ሄልፐ

**ማይግራንት ሄልፐ ማለት ምንድን ነው፤**
ማይግራንት ሄልፐ ከሆም ኦፊስ የተለየ ኣካል ሆኖ ምክር፡ ጉዳዮችን ሪፖርት ማድረግ እና ብቁነት (ኣድቫይስ፡ ኢሹ ሪፖርቲንግ ኢሊጂቢሊቲ/ኤ.ኣይ.ኣር.ኢ(AIRE) የሚባል ብሄራዊ ኣገልግሎት የሚያካሄድ የበጎ ኣድራጎት ድርጅት ነው። ማይግራንት ሄልፐ በጥገኝነት ሂደትዎ እና መብቶችዎ ላይ ገለልተኛ፡ ነጻ ምክር እና መመሪያ ሊሰጥዎ ይችላል። እነሱም በዩኬ ውስጥ ስላሉ ሌሎች አገልግሎቶችን ሊመርዎት ይችላሉ።

**ከማይግራንት ሄልፐ ምን መጠበቅ አለብኝ፤**
ማይግራንት ሄልፐ የገንዘብ ድጋፍ፡ የመኖሪያ ቤት፡ የሕግ ምክር እና ሌሎች በህግ አገልግሎቶች እንዲያገኙ ይረዳዎታል። የጥገኝነት ጥያቄን ቃለ ምልልስ ከማድረግዎ በፊት፡ የጥገኝነት ጥያቄን ሂደት፡ የድጋፍ መብቶችዎን እና ሌሎች አስፈላጊ አገልግሎቶችን (የጤና እንክብካቤ እና የህግ ምክርን ጨምሮ) እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ መረጃ ይሰጡዎታል። አስፈላጊ ከሆነ የቋንቋ አስተርጓሚ ሊያቀብሎት ይችላሉ፡ ይህም ስልክ ጥሪውን ሲጀምሩ ይህን መጠየቅ ይኖርብዎታል።
የማይግራንት ሄልፐ የድጋፍ መስመር በቋንቋዎ ምክር ሊሰጥዎት ይችላል። የማይግራንት ሄልፐ በሚከተሉት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ሊረዳዎት ይችላል፡

- እንዴት ጥገኝነት መጠየቅ እንደሚቻል
- የገንዘብ ድጋፍ
- ህጋዊ ውክልና ማግኘት
- የጥገኝነት ሂደት
- የጤና እንክብካቤ ማግኘት
- የመኖሪያ ቤት ድጋፍ

በማይግራንት ሄልፐ በኩል ስለ ሆም ኦፊስ ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ፡ ነገር ግን ይህ ቅሬታ ከጥገኝነት ጠያቂዎች መኖሪያ ቤት ወይም ከሚሰጠው ድጋፍ ጋር የተያያዘ መሆን አለበት። በመጀመሪያ ማንኛውም ያለብዎት ቅሬታ ማንኛውም ሌላ እርምጃ ወይም አቤቱታ ከማቅረብዎ በፊት በመጀመሪያ ደረጃ በማይግራንት ሄልፐ ቅሬታዎን ማቅረብ አለብዎት።

የጥገኝነት ጥያቄዎን ወይም ስለ የጥገኝነት ጥያቄ ይግባኝ ማቅረብን በተመለከተ የሚቀርቡ አቤቱታዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም፡ እነዚህን ለማሳካት በዚህ ጉዳይ ላይ በተሰጡት ደብዳቤዎች ውስጥ ያሉትን መመሪያዎች መከተል አለብዎት።

ኢ-ቪዛ፡ ኣፕሊኬሽን ረጂስትሬሽን ካርድ (ኤ.ኣር.ሲ) ስህተቶች፡ እንዲሁም የስራ ፈቃድ (ፒ.ቲ.ዳብሊዉ) ጉዳዮች ከሚግራንት ሄልፕ ጋር መነሳት የለባቸውም። ይልቁንም፡ እነዚህን ጉዳዮች ለሚከተሉት አገልግሎቶች ሪፖርት ማድረግ አለብዎት (http://www.gov.uk)

- **ኢ - ቪዛ -** (https://www.gov.uk/evisa/report-error-evisa)
- **ኤ.ኣር.ሲ -** (https://www.gov.uk/government/publications/application-registration-card-arc)
- በጥገኝነት ማመልከቻዎ እየታየ ባለበት ሰአት የመጀመሪያዎቹ 12 ወራት ውስጥ ስራ እንዲሰሩ አይፈቀድልዎትም። ይህ ህገወጥ ተግባር ነው፡ ነገር ግን በጥገኝነት ማመልከቻዎ ላይ ውሳኔ ለማግኘት ከ 12 ወራት በላይ ከጠበቁ የሥራ ፈቃድ ማመልከት ይችላሉ። እርሶ መስራት የሚችሉባቸዉ የሥራ ዓይነቶች ለተወሰኑ የሥራ ዓይነቶች ብቻ የተገደቡ ናቸው። በጥገኝነት ማመልከቻዎ ላይ ውሳኔን በመጠባበቅ ላይ ሳሉ የበጎ ፍቃድ ሥራ መሥራት ይችላሉ፡ ይህም የሚበረታታ ተግባር ነዉ።
- **ፒ.ቲ.ዳብልው -** (https://www.gov.uk/government/publications/working-whilst-an-asylum-claim-is-considered/working-in-the-uk-whilst-an-asylum-case-is-considered)

ማይግራንት ሄልፕ የእርዳታ መስመር ሁሉንም ጥገኝነት ጠያቂዎች ይረዳል፡ እናም እነዚህ የስልክ መስመሮች ብዙ ሰዉ ስለሚደዉል ጥሪዎን ለመመለስ መዘግየት ሊኖራቸው ይችላል። ጥሪዎን በትዕግሥት ይጠብቁ እና በተቻለ ፍጥነት ጥሪዎን ተቀብለዉ ያዋራቿል። ከተቻለ እባክዎን አስቸኳይ ያልሆኑ ጉዳዮችን ***ሪፖርት ለማድረግ ድረ-ገጾችን*** ለመጠቀም ያስቡ።

ማይግራንት ሄልፕ የገንዘብ ድጋፍ እና የመኖሪያ ቤት (የጥገኝነት ጠያቂ ድጋፍ) (ኤ.ኤስ.ኤፍ1/ASF1) ወይም ለተጨማሪ የጥገኝነት ድጋፍ (ኤ.ኤስ.ኤፍ2/ASF2) የማመልከቻ ቅጽ ለመሙላት ሊረዳዎት ይችላል። በሁኔታዎ ላይ ለውጥ ካለ ለሆም ኦፊስ ማሳወቅ ከፈለጉ ይረዱዎታል።

ማይግራንት ሄልፕ ህጋዊ ምክር ወይም ውክልና መስጠት አይችልም። ህጋዊ አገልግሎት እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ መረጃ ሊሰጥዎት ይችላል። በተጨማሪም በሚከተለው ህጋዊ አማካሪ መፈለግ ይችላሉ። (http://www.gov.uk/find-a-legal-adviser)

እንዲሁም የመኖሪያ ቤት አቅራቢ፡ የፋይናንስ አቅራቢ፡ የሆም ኦፊስ ወይም እራሳቸውን ማይግራንት ሄልፕ ቅሬታ ማቅረብ በሚፈልጉበት ጊዜ ማይግራንት ሄልፕ ማነጋገር አለብዎት። በመኖሪያ ቤትዎ ችግሮች ካሉዎት ማይግራንት ሄልፐን ማነጋገር አለብዎት። ይህንን እንዴት ማድረግ እንደሚችሉ ስለ መኖሪያ ቤት ቅሬታ/ኮምፕሌይንት ስለ መኖርያ ቤት ሊያገኙት ይችላል፡ የተደረገው ቅሬታ የጥገኝነት ማመልከቻዎን ውጤት ወይም ድጋፍ እና የመኖሪያ ቤት ድጋፍ ብቁነትዎን ላይ ምንም ተጽዕኖ የለውም።

**ማይግራንት ሄልፕ ከእኔ ምን ይጠብቃል፧**

- ከማይግራንት ሄልፕ ጋር በሚነጋገሩበት ጊዜ፡ በሆም ኦፊስ ሰነዶች ላይ ያለውን የማጣቀሻ ቁጥር ይዘው ያነጋግሯቸዉ።
- ለእርስዎ የተያዘልዎትን ቀጠሮ መገኘት አለብዎት። ከጥያቄዎ ጋር የተያያዙ ማንኛውም መረጃዎችን ወይም ሰነዶችን ይዘው ይምጡ።
- ጓደኛዎን ወይም ቤተሰብዎን በእርስዎ ምትክ ለማይግራንት ሄልፕ እንዲያነጋግሩ ከመጠየቅ ይልቅ በተቻለ መጠን ከማይግራንት ሄልፕ ጋር እራስዎ ለመነጋገር ይሞክሩ። እንግሊዝኛ የማይናገሩ ከሆነ አይጨነቁ፡ የቋንቋ አስተርጓሚዎች አሉ።
- ለማይግራንት ሄልፕ ከመደወልዎ በፊት ወይም ቀጠሮዎ ላይ ከመገኘትዎ በፊት ማስታወሻ ያዘጋጁ፡ ይህም ሁሉም ጥያቄዎችዎ በብቃት እንዲመለሱ ያደርጋል።
- ለአማካሪዎች ጥያቄዎች በተቻለ መጠን ሙሉ ምላሽ ይስጡ። ስለጥያቄዎ ለመርዳት ስለ መጠየቅ ያለባቸውን ጥያቄዎች ስልጠና ወስደዋል።

- በመገናኛ ዘዴዎችዎ ላይ ማንኛውንም ለውጥ ለምሳሌ የስልክ ቁጥር እና የኢሜይል አድራሻ መለወጥ ካለብዎት ያሳውቁ።
- ማይግራንት ሄልፕ ሁልጊዜ ማንነትዎን ያረጋግጣል እና ለሶስተኛ ወገኖች የግል መረጃን በጭራሽ አይገልፅም። ሌላ ግለሰብ ወይም አካል እርሶን በመወከል እርምጃ እንዲወስድ ከፈለጉ ይህን ለማመቻቸት: **ስልጣን የመስጠት ደብዳቤ(ሌተር ኦፍ ኦዉቶሪቲ)** መፈረም ወይም ይህን ለማድረግ **የቃል ፈቃድ** መስጠት ያስፈልግዎታል። ይህንን እንዴት ማድረግ እንደሚቻል ተጨማሪ ምክር ለማግኘት እባክዎ ማይግራንት ሄልፕ ያነጋግሩ። ይፈቃድ ቅጽ እዚህም ማግኘት ይችላሉ: URL: (https://selfserve.migranthelpuk.org/consent-form-third-party-final.pdf)

ማይግራንት ሄልፕ ስድቦችን፡ ማስፈራሪያዎችን ወይም ጠበኛ ባህሪያትን አይታገስም። ሰራተኞቻቸው በስርኣት እና በአክብሮት ያስተናግዱዎታል። እርስዎም በእነሱ ላይ እንደዚህ ዓይነት ተገቢ ባህሪ ማሳየት አይርሱ።

### ማይግራንት ሄልፕን እንዴት ማግኘት ይቻላል

ለማይግራንት ሄልፕ በሚከተሉት መንገዶች ማግኘት ይችላሉ፡
- **ዌብቻት** በማይግራንት ሄልፕ ዌብ ቻት (URL: https://www.timeforstorm.com/CustomChat/MigrantHelp/1/)
- በዌብሳይት ላይ ያለዎትን **ጉዳይ ያቅርቡ:** (URL: https://selfserve.migranthelpuk.org/submit-issue/) (https://selfserve.migranthelpuk.org/submit-issue/)
- **ነፃ የስልክ የእገዛ መስመር** 0808 8010503.

እነዚህ አገልግሎቶች በቀን 24 ሰዓታት፡ በሳምንት 7 ቀናት የሚገኙ ሲሆን ሙሉ የቋንቋ አስተርጓሚ አገልግሎት ይሰጣሉ። እባክዎ ልብ ይበሉ፡ በናፒየር እየኖሩ ከሆነ፡ የማይግራንት ሄልፕ ሰራተኞች በዚያ ይገኛሉ።

ተጨማሪ መረጃ እና በ10 ቋንቋዎች የተተረጎመ ምክር በሚግራንት ሄልፕ ድረገጽ (http://www.migranthelpuk.org/) ይገኛል።

## ክፍል 3 ስለ ጉዳዮች ሪፖርት ማድረግ እና ቅሬታ ማቅረብ

**በመኖሪያ ቤትዎ ወይም በሚሰጥዎት ድጋፍ ላይ ችግር ካለብዎት ወይም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስለሚገኙ ማናቸውም ተቋማት ቅሬታ ማቅረብ ከፈለጉ፡ ይህንን በተቻለ ፍጥነት በማይግራንት ሄልፕ በኩል ማሳወቅ አለብዎት።**

የተነሱ ማናቸውም ቅሬታዎች ወይም ጉዳዮች የጥገኝነት መብትዎን ወይም ቀጣይ ድጋፍዎን አይነኩም ። የምንቀበላቸው ማናቸውም ቅሬታዎች በቁም ነገር እንደሚወሰዱ እና በተገቢው ኤጀንሲዎች እንደሚመረመሩ ስናሳውቆት ምቾት ሊሰማዎት ይገባል። ማንኛውም ሪፖርት የተደረገባቸው ብልሽቶች እንደ የብልሽቱ ምድብ በተጠቀሰው የጊዜ ማዕቀፍ ውስጥ ይስተካከላሉ ። 'የተከሰቱ ብልሽቶችን በጊዜ ገደብ ውስጥ ካልተስተካከለ ጉዳዮን የባሰ እንዲያቀላጥፉት እንደገና እነሱን ማግኘት ኣለባቹ' (http://www.migranthelpuk.org/)

ስለ ማንኛውም የመኖሪያ ቤትዎ ወይም የሚያገኙትን ድጋፍ  ቅሬታ ለማቅረብ በሚፈልጉበት ጊዜ በተቻለ ፍጥነት ማቅረቡን አስፈላጊ ነው። ይህ እኛ የምናቀርበውን አገልግሎት ለማሻሻል ስለሚረዳ ግብረመልስ እና ቅሬታዎችን በደስታ ነዉ የምንቀበለዉ። የቅሬታዉ ሂደት ተጨማሪ ኦፊሴላዊ እርምጃ ከመውሰዳቸው በፊት ማካሄድ ኣለባቸዉ፡ ይህ ደሞ የመኖሪያ ቤት አቅራቢዎች እና/ወይም ሆም ኦፊስ ጉዳያችሁን ለመመርመር እድል እንዲያገኙ ነዉ።

**ስለሚከተሉት ጉዳዮች ማይግራንት ሄልፕን ማግኘት አለብዎት:**

- **የጥገና ጉዳዮች –** በጥገኝነት ጠያቂዎ መኖሪያ ቤት ውስጥ ያሉ ብልሽትን ሪፖርት ለማድረግ። እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ለመኖሪያ ቤት አቅራቢዎ እርስዎን ወክለው ያነጋግራሉ (በገጽ 24 ላይ "ጥገና እና ማሻሻያ" የሚለውን ይመልከቱ)።
- **እርዳታ መጠየቅ –** በጤናዎ እና በጥሩ ሁኔታዎ ወይም በቤተሰብዎ ላይ አደጋ እንዳለ ከተሰማዎት። ይህም ችላ የተባለ ልጅ፡ የቤት ውስጥ ጥቃት፡ ወሲባዊ ትንኮሳ ወይም ብዝበዛ፡ ፀረ-ማህበራዊ ባህሪያት፡ ድህነት ወይም ቤት አልባ መሆን ወይም የአክራሪነት ወይም ጽንፈኝነት ለማሳወቅ ሊሆን ይችላል።
- ማይግራንት ሄልፐ ስለ ጥያቄዎ ወይም ሪፖርትዎ ወደ መኖርያ ቤት አቅራቢዎ ያስተላልፋል፡ እነሱ ደግሞ ለሆም ኦፊስ እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለፖሊስ ማሳወቅ ጨምሮ የእርስዎን ደህንነት ለማረጋገጥ አስፈላጊውን እርምጃ የመውሰድ ሃላፊነት ይወስዳሉ።
- **ቅሬታ –** በ ማይግራንት ሄልፐ፡ በመጠለያ አቅራቢዎ፡ ለጥገኝነት ጠያቂዎች የገንዘብ ድጋፍ አቅራቢ ወይም ለሆም ኦፊስ በሚሰጡት አገልግሎቶች ላይ ቅሬታ ማቅረብ በሚፈልጉበት ጊዜ፡ ማነኛዉ ተጨማሪ ኦፊሲያላዊ እርምጃ ከመዉሰዶ በፊት ማይግራንት ሄልፐ በማነጋገር መርመራ እንዲካሄድ እና ምላሽ እንዲሰጦት ቅሬታ ለማቅረብ መጠየቅ አለብዎት።
- **ግብረ መልስ/አስተያየት –** በጠቅላላው የጥገኝነት ጉዳይዎ ሂደት ውስጥ የሚደረግ ድጋፍ በተከታታይ ለማሻሻል። ለሚግራንት ሄልፐ ስለ አገልግሎታቸው፡ ስለ መጠለያ አቅራቢዎ፡ ስለ ጥገኝነት ጠያቂዎ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ ወይም ስለ ሆም ኦፊስ ያለዎትን ተሞክሮ ሊነግሯቸው ይችላሉ። አስተያየትዎ ለሚመለከተው አካል ይተላለፋል።

ይህንን ለማድረግ በስልክ ቁጥር **0808 8010 503** ይደውሉ፡ **ዌብቻት** ይጠቀሙ ወይም ጉዳይዎን በዚህ መንገድ ያቅርቡ (https://www.timeforstorm.com/CustomChat/MigrantHelp/1/) (https://selfserve.migranthelpuk.org/submit-issue/)

የራስዎን ምግብ ማብሰል የሚችሉበት ቤት ካልሆኑ በስተቀር በመኖሪያ ቤትዎ የስልክ አገልግሎት ማግኘት አለብዎት። ይህንን ለማግኘት እየተቸገሩ ከሆነ እባክዎን በመኖሪያዎ ውስጥ ካሉ የሰራተኞች አባላት አንዱን ያነጋግሩ። እንዲሁም በአከባቢዎ ቤተ-መጽሐፍት/ላይብረሪ ኮምፒተር እና ኢንተርኔት በነፃ ማግኘት ይችላሉ።

ጉዳዩ በቀጥታ ከሚግራንት ሄልፐ ጋር የሚነሳ ይሆናል ወይም የሚመለከተው አገልግሎት ሰጪ እንደሚመረምረው ያረጋግጣሉ። አማካሪዎቹ ጉዳዩ ምን ያህል ፈጣን መፍትሄ እንደሚያገኝ ምን ያህል ግዜ መጠበቅ እንዳለብዎ የጊዜ ሰሌዳ ይሰጡዎታል።

ምንም እንኳን በቀጥታ ከመኖሪያ ቤትዎ ተሞክሮ ጋር ስለሚዛመዱ ማናቸውም ጉዳዮች (ለምሳሌ ምግብ፡ የሽን ቤት እቃዎች እና አስፈላጊ ነገሮች መገኘት፡ እንደ የልብስ ማጠቢያ ያሉ ኣገልግሎት ያሉ መገልገያዎች ወዘተ) በቀጥታ የመኖሪያ ቤቱን ሰራተኞች መጠየቅ ቢችሉም፡ ስለ የጥገና ጥያቄዎችን ወይም የገንዘብ ድጋፍ ጉዳዮችን በዚህ መንገድ አያቅቀርቡ። ይልቁንም ጉዳዩ በይፋ መመዝገብ እንዲቻል ወደ ማይግራንት ሄልፐ ማሳወቅ አለቦት። ይህ ደሞ ጉዳዩ በይፋ እንዲመዘገብ እና ኣስፈላጊዉን መፍትሄ እንዲደረግ ከትትል መደረግ እንዲቻል ነዉ።

## የአስፓን እና የክፍያ ጉዳዮች

ከአስፐን ካርድዎ ጋር በተያያዘ እርዳታ ከፈለጉ፡ **የድጋፍ አቅራቢውን የቅድመ ክፍያ የገንዘብ አገልግሎት (ፕሪ ፔይድ ፋይናንሻል ሰርቪስስ ፒ.ኤፍ.ኤስ)** በስልክ ቁጥር **0800 246 1327** ማግኘት ይችላሉ። አንዴ ከተገናኙ በኋላ፡ ድጋፉ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ሶስት አማራጮች ሊሰጥ ይችላል፡

- ፒን ማሳወቅ/ማሳየት
- ስለ ያለው የገንዘብ መጠን ጥያቄ
- የጠፋ እና የተሰረቀ - ካርድ መቆለፍ

ይህ አገልግሎት እንግሊዝኛን ጨምሮ በ10 ቋንቋዎች ይገኛል። **በአሁኑ ጊዜ የሚከተሉት የቋንቋ አማራጮች አሉ፡ እንግሊዝኛ፡ አልባኒያኛ፡ አማርኛ፡ አረብኛ፡ ቻይንኛ፡ ፋርስኛ፡ ኩርድኛ፡ ፓስቶ፡ ፑንጃቢ፡ ትግርኛ፡ ኡርዱ።**

ከአስፓን ካርድዎ ወይም ከጥገኝነት ክፍያ ጋር የተያያዘ ሌላ ጉዳይ ካለዎት፡ ሚግራንት ሄልፕን ማነጋገር አለብዎት፡ እነሱም ጉዳዩን በእርስዎ ምትክ ለሚመለከተው አካል ያቀርባሉ።

## ቅሬታ ስለ አገልግሎት አቅራቢዎች

ከመኖሪያ ቤትዎ አቅራቢ፡ ከድጋፍ ክፍያ አቅራቢ ወይም ከማይግራንት ሄልፕ የሚያገኙት አገልግሎት ጋር የተያያዘ ቅሬታ በማይግራንት ሄልፕ በኩል መቅረብ አለበት። ይህንን ለማድረግ በ **0808 8010 503** ይደውሉ፡ **ዌብቻት** ይጠቀሙ ወይም ጉዳይዎን በዚህ መንገድ ያቅርቡ አገልግሎት ሰጪው በ 5 የስራ ቀናት ውስጥ ቅሬታዎን ለመፍታት እና ምላሽ ለመስጠት ይሰራል። በሚመለከተው አገልግሎት ሰጪ መፍታት ካልቻለ ወይም በመልሱ ደስተኛ ካልሆኑ፡ ማይግራንት ሄልፕ ቅሬታዎን ወደ ሆም ኦፊስ ይልካል። (https://www.timeforstorm.com/CustomChat/MigrantHelp/1/) (https://selfserve.migranthelpuk.org/submit-issue/)

በአገልግሎት አቅራቢው ላይ ቅሬታ ወደ ሆም ኦፊስ ሲላክ፡ ይህ ቢሮ በ 20 የሥራ ቀናት ውስጥ ምላሽ ለመስጠት ዓላማ አለው። በእኛ ምላሽ ካልረኩ ቅሬታዎን በኢሜል ወይም በጽሑፍ መልእክት በ ፒኦ ቦክስ 6147, SHEFFIELD, S2 9JD መልስ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በሶስት ወራት ውስጥ መላክ ይችላሉ። ሆኖም ግን ቅሬታዎ እንዴት እንደተስተናገደ ኣይ.ኢ.ሲ ከግምት ውስጥ ማስገባት የሚችል ቢሆንም፡ የዉል ግዴታ የሌለዉ ኣገልግሎት በተመለከተ የሚቀርብ ቅሬታ ሊመለከተ እንደማይችል ልብ ይበሉ። (mailto:iec@homeoffice.gov.uk)
ቅሬታዎን ለ ኣይ.ኢ.ሲ ለማስተላለፍ ከወሰኑ፡ ያቀረቡትን ማንኛውንም ማስረጃ እና የመጀመሪያ ቅሬታዎን ሲያቀርቡ የሆም ኦፊስ የሰጠዎትን ምላሽ ማቅረብ ይጠበቅብዎታል።

ስለ ነፃ የቅሬታ መመርመሪያ እና ስለ አይ.ኢ.ሲ ቅሬታዎን ማቅረብ የሚሰጥ መመሪያ ተጨማሪ መረጃ በ Gov.uk ድረገጽ (https://www.gov.uk/guidance/make-a-complaint-to-the-independent-examiner-of-complaints) ላይ ማግኘት ይቻላል።

ለቅሬታዎ አሁንም በ አይ.ኢ.ሲ የተሰጠ ምላሽ ካልረኩ ይህ ለፓርላማዊ ኣገልግሎት ጤና እና ኣስታራቂ ኦምቡስማን ሊላክ ይችላል። ኦምቡስማን በ ኤንኤችኤስ፡ በመንግስት ክፍሎች እና በሌሎች የህዝብ ተቋማት ያልተፈቱ ቅሬታዎችዎ የመጨረሻ ውሳኔዎችን ይሰጣል። አገልግሎቶቻቸው ለሁሉም ሰው ነፃ ናቸው። በዚህ ኦምቡስማን ላይ ቅሬታ ለማስገባት በአካባቢዎ ያለውን ኤምፒ ማነጋገር ኣለቦት እና እሱም እርሶን ወክሎ ሪፈር ሊሎት እንደሚችል ልብ ይበሉ። ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት በ 0345 015 4033 ይደውሉ ወይም ይጎብኟቸዉ (http://www.ombudsman.org.uk)

## ቅሬታ ስለ ሚሰጦት ድጋፍ

ስለ ሆም ኦፊስ ከማይግራንት ሄልፕ ጋር ቅሬታ በሚደረግበት ጊዜ፡ ይህ 20 የሥራ ቀናት ውስጥ መርመራ ተደርጎበት ምላሽ እንዲሰጥ ለሚመለከተው ቡድን ጋር ያጋራል። በሚሰጠው ምላሽ ካልረኩ፡ ይህ እንዲገመገም ወደ ማዕከላዊ የቅሬታዎች ቡድን (ሲ.ሲ.ቲ) ለማስተላለፍ መብት አላችሁ። ይህንን እንዴት ማድረግ እንደሚችሉ ምክር ማግኘት ይችላሉ: Complaints procedure - UK Visas and Immigration - GOV.UK

## ለሆም ኦፊስ በሌላ መንገድ እንዴት ቅሬታ ማቅረብ እችላለሁ፤

የተጠቃሚ ተሞክሮ በተሻለ ለመረዳት እና አገልግሎቱን ለማሻሻል የሚረዱ ቅሬታዎችን በደስታ እንቀበላለን። በ ማይግራንት ሄልፕ በኩል ቅሬታ ማቅረብ በማንኛውም የድጋፍ ማመልከቻ ወይም የጥገኝነት ማመልከቻ ውጤት

ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደማያሳድር እና ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ ርዝመት ላይ ተጽዕኖ እንደማያሳድር ልናረጋግጥልዎ እንወዳለን። የሚከተሉትን ኣይነት ሁኔታዎች ላይ ቅሬታዎን በቀጥታ ለሆም ኦፊስ ማቅረብ ይችላሉ፡

- ቀደም ሲል በማይግራንት ሄልፕ ቅሬታ አቅርበው በተሰጠዎት መልስ ላይ ያለዎት ያለመርካት ጉዳይ ለማይግራንት ሄልፕ ቢሮ አሳውቀው እንደገና እስካሁን በውጤቱ ካልረኩ ወይም
- ይህ ለማይግራንት ሄልፕ መፍታት አይገባውም ብለው የሚያስቡት ቅሬታ ካለዎት።

***ሆም ኦፊስ ወደ ማይግራንት ሄልፕ መሄድ የሚጠበቅበትን ቅሬታ ከተቀበለ፡ ቅሬታውን ወደ ሚግራንት ሄልፕ ያስተላልፉል።*** *ወደ ሆም ኦፊስ ቅሬታ ለማቅረብ የሚከተለውን ይጎብኙ፡* URL (https://www.gov.uk/government/organisations/uk-visas-and-immigration/about/complaints-procedure)
*ወይም ደግሞ በሚከተለው አድራሻ ይጻፉልን:*

**Complaints Allocation**
**Customer Correspondence Hub**
**4th Floor 2 Ruskin Square**
**Dingwall Road**
**Croydon CR0 2WF**

## ክፍል 4 የመኖሪያ ቤቶች መረጃ እና መለኪያዎች

**የመኖሪያ ቤት አቅራቢዎቻችን የተለያዩ የመኖሪያ ቤት ኣይነት አሏቸው፡ እና በሚከተሉት ውስጥ ሊመደቡ ይችላሉ፡**

**ሆቴል**
ይህ ዓይነቱ የመኖሪያ ቤት አብዛኛውን ጊዜ በአንድ አገልግሎት ተጠቃሚ እና ቤተሰቦች የሚኖሩበት ሲሆን ምግብ ጭምር የሚያቀርብ የመኖርያ ኣይነት ነዉ። መኖሪያ ቤት ያለ ምርጫ ነዉ የሚሰጠዉ እና እርስዎ በሚኖሩበት ክፍል ውስጥ ከሌሎች ጋር መጋራት ሊጠበቅቦት ይችላል። ፆታዎ ተመሳሳይ ከሆነ ከጓደኛዎ ወይም ከቤተሰብዎ ጋር በአንድ ክፍል ውስጥ እንዲቆዩ ይመከራል። የአገልግሎት ተጠቃሚዎች በአንድ ክፍል ውስጥ ከሚኖሩት ሰው ጋር ተመሳሳይ ቋንቋ የሚናገሩ እንዲሆኑ ለማድረግ እያንዳንዱ ጥረት ይደረጋል። እያንዳንዱ የጋራ ኣገልግሎት ባሉበት እያንዳንዱ ቦታ፡ ፆታ የሚለይ ለያንዱ ፆታ የተለየ የመጸዳጃ ቤት ይኖራል።

**ዋናዉ የመጀመሪያ የመኖሪያ ቤት**
ይህ ዓይነቱ የመኖሪያ ቤት ብዙውን ጊዜ በመደበኛነት የምግብ ኣቅርቦት ባላቸው (በቀን 3 ጊዜ የምግብ ኣቅርቦት ባላቸው) ለብቻቸዉ ያሉትን የአገልግሎት ተጠቃሚዎች እና ቤተሰቦችን የሚሰጥ ነዉ። እያንዳንዱ ጾታ የራሱ የመጸዳጃ ቤት መገልገያዎች አሉት እና የሆም ኦፊስ በጋራ የመኖር ህግን ግምት ዉስጥ ያስገባ የጋራ መኝታ ቤት ሊኖር ይችላል።

**ሌሎች (እንደ አዳራሾች ወይም የወታደራዊ መጠለያዎች የነበረ ቦታ ጨምሮ ያሉ ትላልቅ የጋራ መኖሪያ ቦታዎችን ጨምሮ)**
ትላልቅ ቦታዎች – እንደ ዌዘርስፊልድ ያሉ - ዋስትና ያለዉ እና ተግባራዊ የሆነ መኖርያ ቤት ሁሉመዳያዊ የጤና እንክብካቤ ኤንኤችኤስ ጫና እፎይታ ለመስጠት፡ የመመገቢያ መገልገያዎችን፡ በአካባቢው ያሉ ከተማዎች መጓጓዣን፡ የደህንነት ድጋፍን እና 24/7 የጸጥታ ኣከባሪዎች ያቀርባል። እነኚ ቦታዎች እስር ላይ የሌሉ ለብቻቸዉ የሆኑ እድሜያቸዉ ከኣስራ ስምንት ኣመት በላይ የሆኑት ወንድ ጥገኝነት ጠያቂዎችን ብቻ የሚያስተናግዱ ናቸዉ።

### ህጎች እና መመሪያዎች

በሚኖሩበት መኖሪያ ቤት ውስጥ በደምብ እንዲዋሃዱ እና ለሌሎች ነዋሪዎች ጋር የሚፈጠረውን ማንገላታት ለመቀነስ የሚከተሉትን ማድረግ አለብዎት፡

**እርስዎ ማድረግ ያለብዎት፡**

- ለጤንነትዎ እና ለደህንነትዎ ይጠንቀቁ እና ሁሉንም መሳሪያዎች በጥንቃቄ ይያዙ።
- የሰዉ ጾታ፡ ጾታዊ ማንነት፡ ዘር፡ ብሄር፡ ቋንቋ፡ ዜግነት፡ ሃይማኖት፡ አካል ጉዳተኝነት፡ ጾታዊ ዝንባሌ ምንም ይሁን ምን በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች እና ለመኖሪያ ቤቱ ሰራተኞች በአክብሮት መያዝ።
- ሌሎች ነዋሪዎችን እና ሰራተኞችን በአክብሮት በጭዋነት መያዝ
- የጥገና ወይም የማስተካከያ ጉዳዮችን ሲያስተውሉ ወዲያውኑ ለማይግራንት ሄልፕ ያሳውቁ።
- የመኝታ ክፍል፡ የመኖሪያ ቦታ ወይም የጋራ መኖሪያ ቦታ ከሌሎች ጋር የሚጋሩ ከሆነ ማንኛውንም የግል ንብረትዎን በአስተማማኝ መንገድ ያስቀምጡ።
- እያንዳንዱ መጸዳጃ ቤት ከተጠቀሙ በኋላ ውሃ ማፍሰስ አለብዎት፡ ነገር ግን እንደ የሕፃናት ናፒ ወይም የጽዳት ምርቶች ያሉ ነገሮችን በመጸዳጃ ቤት ውስጥ አያስገቡ።
- መኖሪያ ቤቱን በየጊዜው ማጽዳት ወይም የጽዳት አገልግሎት በሚሰጥበት ቦታ፡ ይህንን ለማመቻቸት መሬቱን ወይም አካባቢውን ማስተካከል።
- በቤት ውስጥ እርጥበት እንዳይፈጠር መስኮቱን ሁል ጊዜ ይክፈቱ።
- በሌሊት እና ከቤት ሲወጡ በሮች እና መስኮቶች መዘጋታቸውን ያረጋግጡ።

**እርስዎ ማድረግ የሌለብዎት ነገሮች፡**

- በተለይ ከምሽቱ 11 ሰዓት እስከ ጠዋቱ 8 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ ድምጽ አለማድረግ
- በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ አለማጨስ
- በክፍልዎ ውስጥ ምግብ ማብሰል አይፈቀድም (ምግብ በሚቀርብባቸው ቦታዎች ውስጥ ያሉትን ማለት ነው)
- በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ የቤት እንስሳት ወይም እንስሳት መያዝ የለብዎትም
- እርስዎን ለመጎብኘት የመጡ ሰዎች በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ እንዲያድሩ መፍቀድ የለብዎትም።
- በመኖሪያ ቤቱ ላይ ዉድመት የሚያደርስ ተግባር ማድረግ አይፈቀድም
- ከተመደበው የመመገቢያ ቦታ ወደ ክፍልዎ ምግብ መውሰድ አይፈቀድም (ከመኖሪያ ቤቱ ይህንን ተግባር እንደሚፈቅድ እስካልተነገረዎት ድረስ)
- በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ ማንኛውም ዓይነት ለውጥ ወይም ጥገና ወይም የኤሌክትሪክ ስራ መስራት አይፈቀድም።
- የጭስ ማሳወቂያ ኣላርም እንዳይሰራ ማድረግ
- በህንፃው ውስጥ የተከለከሉ መድኃኒቶችን ወይም አደንዛዥ ዕፅን መያዝ ወይም መጠቀም አይፈቀድም
- ሌሎች ነዋሪዎችን መረበሽ አይፈቀድም
- በማንም ሰው ላይ ተገቢ ያልሆነ ባህሪ ወይም ቃላት መጠቀም አይፈቀድም
- የሌሎች ሰዎችን ደብዳቤ መክፈት አይፈቀድም
- የኤሌክትሪክ ሶኬት ከመጠን በላይ መጫን እና ሁሉም የኤሌክትሪክ መሳሪያዎች በጥሩ ሁኔታ ላይ መሆናቸውን ማረጋገጥ።
- በመኝታ ክፍሎች ውስጥ ምግብ ማብሰል አይፈቀድም

## በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ እንዲገኙ የሚጠበቁ መገልገያዎች

**በመጀመሪያው መኖሪያ ቤት ውስጥ የሚከተሉት ነገሮች መቅረብ አለባቸው**

**ከሚከተሉት ዝርዝሮች ውስጥ ማንኛውም ነገር ካልተሰጠዎት ወይም ከእነዚህ ዝርዝሮች ውስጥ ማንኛውም ንብረት ከጎደለ ወይም ከተበላሸ ለማይግራንት ሄልፕ ማሳወቅ አለብዎት።**

## የመጸዳጃ መገልገያዎች

**የግል ክፍል ውስጥ መጸዳጃ ቤት ወይም ቢያንስ አንድ ጾታ የለየ መጸዳጃ ቤት በ 5 ሰዎች መካከል የሚኖር ሲሆን ይህም የሚከተሉትን ያካትታል፡**

- ባዝ እና/ወይም ሻወር አስፈላጊ ከሆነ ውሃ የማያስገባ መሸፈኛ ያካትታል (ለምሳሌ የሻወር መጋረጃ)
- የእጅ መታጠቢያ
- መጸዳጃ ቤት

## ምግብ

**የምግብ አቅርቦት ያለው መኖሪያ ቤት፡**

- በቀን ቢያንስ **3 ጊዜ ምግብ** (ቁርስ፡ ምሳ እና የምሽት ሰአት ምግብ እራት) ማቅረብ፡ ቢያንስ አንድ ትኩስ፡ አንድ ቀዝቃዛ አማራጭ እና አንድ የቬጀቴሪያን አማራጭ እንዲሁም ከእያንዳንዱ ምግብ ጋር **የለስላሳ መጠጥ** አገልግሎት
- ለብዙ ሰዎች ለእያንዳንዱ ሰው የሚመርጠውን ጣዕም እና ምርጫን ማርካት ከባድ እንደሆነ ይገንዘቡ። በመኖሪያ ቤትዎ ውስጥ የሚቀርቡ የምግብ ዝርዝር የምግብ ተጽእኖ ለመፍጠር ስለሚቀርበው ምግብ አስተያየት መስጠት ከፈለጉ ለማይግራንት ሄልፕ በማሳወቅ ወይም በቦታው ላይ ላሉት ሰራተኞች በማሳወቅ ያድርጉ።
- ለህጻናት እና ለታዳጊዎች የሚሰጠው የምግብ አገልግሎት ከተገቢው ምግብ ጋር፡ እንደ አስፈላጊነቱ የህጻናትን እና የነፍሰ ጡር ሴቶች የሚያስፈልግ የምግብ ይዘት ለማሟላት ተጨማሪ ምግብ ማቅረብ።
- ልዩ የአመጋገብ ፍላጎቶችን፡ ባህላዊ ወይም ሃይማኖታዊ ፍላጎቶችዎን የሚያሟሉ አማራጮችን እና ለአገልግሎት ተጠቃሚዎች በቀን ሶስት ግዜ የሚሰጠዉ ምግብ በቂዊ በማይሆንበት ግዜ ተጨማሪ ምግቦችን ማቅረብ። እባክዎን የአገልግሎት አቅራቢው ፍላጎቶችዎን በአግባቡ ለሟሟላት እንዲችል ከአጠቃላይ ሐኪም ከጂፒ ወይም ከሕክምና ባለሙያ ማስረጃ ማቅረብ አስፈላጊ መሆኑን ልብ ይበሉ።
- በመደበኛዉ የምሳ አገልግሎት ሰአት መገኘት በማይችሉበት ሰአት (ለምሳሌ፡ በበጎ ፈቃደኝነት ስራ፡ ትምህርት፡ የሕክምና ቀጠሮዎች ምክንያት) ሌላ አማራጭ ለማዘጋጀት በተቻለ ፍጥነት ለአገልግሎት አቅራቢዎ ያሳውቁ።

**ምግብዎን በራስዎ የሚያዘጋጁበት መኖሪያ ቤት:**

- በ 5 ሰዎች መካከል ቢያንስ 1 ኩሽና መኖር አለበት ይህም የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡
- የምግብ ማብሰያ መሳሪያዎች
- ፍሪጅ እና ፍሪዘር፡ የማብሰያ ምድጃ ወይም ኦቨን እና ሆብ።
- ንጹህ የምግብ ማብሰያ ቦታዎች እና አከባቢዎች
- ሲንክ
- የንጽህና መጠበቂያ መሳሪያዎች
- ከጤና እና ደህንነት ጋር የተያያዙ ማናቸውም ጥያቄዎች እና ስጋቶች በመጀመሪያ ለማይግራንት ሄልፕ ማሳወቅ አለብዎት፡ ይህም አገልግሎት ሰጪው እንዲያውቅ እና ምርመራ እንዲጀምር ያስችላል።

## መኝታ ክፍል

**ሁሉም የመጀመሪያ መኖሪያ ቤት፡**

- በቤቱ ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች የሚሆኑ ኣልጋዎች (ነጠላ ወይም ዳብል ኣልጋዎች) እንዲሁም ለሕፃናት እና ለታዳጊዎች የሚሆኑ ኣልጋዎች (ኮት)።
- 1 ቁምሳጥን ወይም ሌላ የልብስ ማንጠልጠያ ይህም በእያንዳንዱ ክፍል ወይም ክፍሉ ግንኙነት የሌላቸው አዋቂ ሰዎች በጋራ የሚኖሩበት ከሆነ 1 ለእያንዳንዳቸው።
- 1 ተመዛዥ ሣጥን ወይም ሌላ መፍትሄ ለማከማቻ መደርደሪያ የሚሆን ይህም በእያንዳንዱ ክፍል ወይም ክፍሉ ግንኙነት ለሌላቸው አዋቂ ሰዎች በጋራ የሚኖሩበት ከሆነ 1 ለእያንዳንዳቸው።
- በመስኮት ላይ የተተከለ መጋረጃ ወይም ሽፋን።

## የሳሎን ክፍል እና የጋራ ቦታዎች

**የምግብ አቅርቦት ያለው መኖሪያ ቤት፡**

- የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ብዛይ የሚያስተናግድ በቂ የመመገቢያ ቦታዎች እና ምቹ መቀመጫዎች መኖር አለባቸው።

**ምግብዎን በራስዎ የሚያዘጋጁበት መኖሪያ ቤት፡**

- ጠረጴዛ፡ ለአንድ ሰው 1 የመመገቢያ ወንበር እና ለአንድ ሰው 1 አርምቼር መኖር።

**በሁሉም የመጀመሪያ መኖሪያ ቤት ውስጥ፡**

- ለመዝናኛ ተግባራት ምክንያታዊ የሆኑ ጠረጴዛዎች እና ምቹ መቀመጫዎች መኖር

### አገልግሎቶች

**በሁሉም የመጀመሪያ መኖሪያ ቤት፡**

- ምክንያታዊ የሆነ የንጹህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት (በዩኬ ውስጥ የቧንቧ ውሃ ለመጠጣት ደህንነቱ የተጠበቀ እንደሆነ እና የጠርሙስ ውሃ ማቅረብ አስፈላጊ እንዳልሆነ ያስተውሉ)
- ምክንያታዊ የሆነ የልብስ ማጠቢያ አቅርቦት (ለምሳሌ፡ የልብስ ማጠቢያ አገልግሎት ወይም የልብስ ማጠቢያ ማሽን)
- የታጠበ ልብስ ማድረቅያ መስጫ (በጠየቁበት ጊዜ)
- የልብስ መተኮሻ ሰሌዳ እና የልብስ መተኮሻ
- አስፈላጊ ከሆነ የሕፃናት እንክብካቤ መሳሪያዎች፡ ኣልጋ(ኮት) እና ሃይቼር እንዲሁም ከ 1 አመት በታች ለሆኑ ሕፃናት የሚጠቀሙባቸዉ እቃዎች የማምከንኛ መሳሪያዎች (እንዲሁም ናፒስ) ጨምሮ
- የጭስ እና ካርቦን ሞኖክሳይድ ማሳወቅያ መሳሪያዎች
- ሁሉም መኖሪያ ቤቶች የጭስ ማሳወቅያ ደወል አላርም (በእያንዳንዱ መኖሪያ ቤት ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ ደረጃ) እንዲሁም የካርቦን ሞኖክሳይድ ማሳወቅያ አላርም (በጋዝ ወይም በሶሊድ ፊውል ያለው መኖሪያ ቤት) ሊኖራቸው ይገባል።
- የቴሌቪዥን እና የ ዋይፋይ አቅርቦቶች፡ ይህ በኮንትራቱ የተሸፈኑ አይደሉም ስለሆነም እነዚህ የግድ መቅረብ የለባቸውም፡ ነገር ግን የመኖሪያ ቤቱ አቅራቢ የራስዎን ምግብ በሚያበስሉበት ቤት ውስጥ የማይኖሩ ከሆነ መልዕክቶችን ለመለዋወጥ የሚያስችል አንዳንድ መንገዶችን ሊያቀርብልዎ ይገባል ። ይህ የሞባይል ወይም የኮምፒተር ስርዓት ወይም ዳታ ያለዉ ሲምካርድ ሊሆን ይችላል። ለተጨማሪ መረጃ የእንግዳ መቀበያ/ ሪሴፕሽንን ያነጋግሩ።.

**የመኖሪያ ቤት አቅራቢው ወደ መኖሪያ ቤቱ በሚገቡበት ጊዜ አዲስ የግል ጨርቃ ጨርቅ ሊያቀርብልዎት ይገደዳል።**

**የሰውነት መታጠቢያ ፎጣ**
2 (ለአንድ ሰው)

**የፊት ፎጣ**
2 (ለአንድ ሰው)

**ኣንሶላ**
2 (ለአንድ ሰው)

**ብርድ ልብስ እና ዱቬት**
2 / 1 (ለአንድ ሰው)

**የእጅ ፎጣ**
2 (ለአንድ ሰው)

**የኩሽና የሻይ ፎጣ**
(ምግብዎን በራስዎ እያበሰሉ የሚኖሩበት የመጀመሪያ መኖሪያ ቤት ብቻ)

1 (ለአንድ ሰው)

**ትራስ እና የትራስ ጨርቅ**
2 ለእያንዳንዳቸው (ለአንድ ሰው)

**የዱቬት ጨርቅ**
2 (ለአንድ ሰው)

## ተጨማሪ ንብረቶች

- ወደ መኖሪያ ቤት የሚወስዷቸው ተጨማሪ ነገሮች እና ንብረቶች የእራስዎ ኃላፊነት ናቸው። የመኖሪያ ቤት አቅራቢዎ ለእነዚህ እቃዎች ምንም አይነት ኃላፊነት ወይም ተጠያቂነት አይወስድም።
- ተንቀሳቃሽ ማሞቂያ አይፈቀድልዎትም፡ ማንኛውም አደገኛ ወይም ዋስትና የሌለዉ እቃ እንዲያስወግዱት ይጠየቃሉ።

የመኖሪያ ቤት አቅራቢዎች ማቅረብ **የማይጠበቅባቸው** አንዳንድ የተለመዱ ነገሮች፡

- የግል ስልክ (ነገር ግን የጋራ የስልክ ኣገልግሎት መቅረብ አለባቸው)
- ብሮድባንድ/ዋይፋይ ኮኔክሽን
- ቴሌቪዥን/ቲቪ
- ቫክዩም ክሊነር (ነገር ግን የቆሻሻ መያዣ እና ብሩሽ ማቅረብ አለባቸዉ)

ከመደበኛው የድጋፍ መጠን በላይ የሚያስወጣ ልዩ ሁኔታ ካለብዎት፡ ተጨማሪ ድጋፍ ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ለበለጠ መረጃ ለማይግራንት ሄልፐ ይደውሉ።

## አገልግሎቶች

የጋዝ፡ የውሃ እና የኤሌክትሪክ አቅርቦቶች ይሰጡዎታል። አካባቢዎን በደንብ ይወቁ እና የእነዚህን አገልግሎቶች አጠቃቀም በትክክል ይከታተሉ። የቤቱ ኦፊሰር ኣገልግሎቶቹን እንዴት እንደሚጠቀሙበት መመርያ ይሰጦታል፡ ይህም የኤሌክትሪክ መቆጣጠሪያዎች የት እንደሚገኙ እና ማሞቅያዉ እንዴት ኣድርገዉ እንደሚጠቀሙበት የመሳሰሉ ናቸዉ። የአገልግሎት አቅራቢውን መለወጥ የለብዎትም።

## የጤና ሰርቲፊኬት (ኤችሲ2)

የሴክሽን 95 ድጋፍ ከተሰጠዎት ብኋላ፡ የ ኤችሲ2 ሰርተፊኬት የማግኘት መብት ይኖርዎታል (ወይም በሴክሽን 4 ላይ ላሉት፡ የ ኤችሲ1 ሰርተፊኬት)። ይህ የሚከተሉትን ለማግኘት ሊያገለግል ይችላል፡

- የ ኤንኤችኤስ የጥርስ ሕክምና
- የ ኤንኤችኤስ ዊግ እና የጨርቅ ድጋፍ
- የዓይን ምርመራ፡ መነጽር፡ ኮንታክት ሌንስ፡ ወይም ደግሞ
- በሐኪም (ጂፒ ወይም የሆስፒታል ሐኪም)፡ የዓይን ሐኪም ወይም የጥርስ ሐኪም ሪፈር ከተባሉ፡ የ ኤንኤችኤስ ህክምና ለማግኘት መጓዝ።

ይህ ሴክሽን 95 ድጋፍ ሲቀበሉ በራሱ ኣዉቶማቲክ ይላክሎታል እና ከዚያ በኋላ በየ 6 ወሩ በኣዉቶማቲክ ይታደሳል። ይሁን እንጂ፡ ድጋፍ ቀባይነት ካገኘበት ጊዜ ጀምሮ በ 3 ሳምንታት ውስጥ ኤችሲ2 ካልመጣላቹ፡ ወደ 300 330 1343 ወቅጣ ወደ ኤንኤችኤስ በመደወል ተጨማሪ ምክር ማግኘት ይችላሉ። እነዚህ መስመሮች ከሰኞ እስከ አርብ ከ ጥዋት 8 ሰኣት እስከ 6 ሰኣት የከሰአት እና ቅዳሜ ከ ጥዋት 9ሰኣት እስከ 3ሰኣት የከሰኣት ድረስ ይሰራሉ። ይህን ወደ ማይግራንት ሄልፐም ሪፖርት ማድረግ አለብዎት።

በሴክሽን 4 ውስጥ ድጋፍ ያሉ ከሆነ የ ኤችሲ1 ቅጽ መሙላት አስፈላጊ ነው። ይህ በአከባቢው የሚገኝ ፋርማሲ ወይም በ ኤንኤችኤስ ድረ ገጽ/የእውቂያ ማዕከል በኩል ማግኘት ይችላሉ እና እዛ የ ኤችሲ1 ቅጽ ለማጠናቀቅ እገዛ

መጠየቅ ይችላሉ። በኦንላይን ወደ nhsbsa.nhs.uk ያመልክቱ። አስቸኳይ ሕክምና ወይም መድሃኒት ከፈለጉ የ ኤን.ኤች.ኤስ.ቢ.ኤስ.ኤ(NHSBSA) ምክር ከዶክተሩ የመድሃኒት ማዘዣ ደብዳቤ በስተጀርባ የሚገኝ ምህረት(መተዉ) ሳጹን ምልክት በማድረግ፡ እናም ፋርማሲዉ ያለ ማስረጃ እንደማይሰጦት ካሳወቀት ወደ የድጋፍ መስመሩ መደወል ነዉ። የ ኤን.ኤች.ኤስ.ቢ.ኤስ.ኤ ምክር እዚህ ማግኘት ይችላሉ (https://www.nhsbsa.nhs.uk/)

## የመኖሪያ ቤት ምርመራ

### <u>እራሱን የቻለ የመጀመሪያ የመኖሪያ ቤት</u>

**መኖሪያው ለእርስዎ ምቹ እና ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ እራሱን የቻለ የመጀመርያ መኖሪያ ቤቱ(እርሶ እና ቤተሰቦ ብቻ የሚኖሩበት ቤት) ላይ ምርመራ ይካሄዳል።** መኖርያ ቤት አቅራቢዉ በቤትዎ ውስጥ ማንኛውም ጉድለቶች መኖራቸውን ለማወቅ እና ለመጠገን ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ መኖሪያውን መመርመር ይጠበቅበታል።

ምርመራው ከሚካሄድበት ቀን እና ሰዓት ቢያንስ 5 ቀናት በፊት እርሶ በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ እንዲጠብቋቸዉ ይነገራሉ። የመኖሪያ ቤት አቅራቢው እርስዎ በቤት ውስጥ ባይገኙም እንኳን መኖሪያ ቤቱን ይመረምራል።

**በምርመራው ወቅት ምን ይከሰታል፧**
ቤቱን የሚመረምር ሰዉ ሁል ጊዜ በሩን ማንኳኳት እና መልስ እስኪሰጥዎት መጠበቅ አለበት። በሩን እንዲከፈትላቸዉ ሳይጠብቁ በሩን በራሳቸዉ መክፈት የለባቸውም። እርሶ በቤት ውስጥ ሳሉ የራሳቸውን ቁልፍ መጠቀም የለባቸውም። ስለ መኖርያ ቤቱ ያነጋግሩዎታል እና ጉድለት ካለ ይፈትሹዎታል። ማንኛውም ጉድለት ከተገኘ ጥገና ይከናወናል። ለመርማሪው ግልፅ ያልሆነ ማንኛውም ጉድለት መታወቅ አለበት።

የአገልግሎት አቅራቢዎች፡ ወይም ሆም ኦፊስ የግል እቃዎችዎን የመፈተሽ መብት አላቸው፡ ነገር ግን መኖሪያውን ለቀው ከሄዱ እና የግል እቃዎችዎን ትተዉ ከሄዱ እነዚህ ዕቃዎች በአገልግሎት አቅራቢው በአንድ ሻንጣ በመሰብሰብ እስከ 28 ቀናት በአጭር ጊዜ ማከማቻ ተቋም ውስጥ ይቆያሉ እናም በዚህ ጊዜ ውስጥ ካልወሰዳቹት እቃዎቹ ይጣላሉ።

**ምርመራውን የሚያካሂደው ማነው፧**
የመኖሪያ ቤቱ ምርመራ ቢያንስ በየወሩ በመኖሪያ ቤትዎ አቅራቢ ይካሄዳል። አንድ ሰው ከሆም ኦፊስ ወይም ከካውንስል የመኖሪያ ቤትዎ አቅራቢዉ ማሟላት አለበት የሚባሉትን መስፈርቶች ማሟላቱን ለማረጋገጥ ይህንን ምርመራ ሊያካሂድ ይችላል።

**በሆቴል/የመጀመሪያ መኖሪያ ቤት ውስጥ የምኖር ከሆነስ፧**
የመጀመሪያ መኖሪያ ቤቶች ብዙ ዓይነት መስፈርት አሏቸው፡ ለምሳሌ ምግብ የሚቀርብባቸው መኖሪያ ቤቶች፡ ሆቴሎች እና ሆስቴሎች። እነዚህ ቦታዎች በየ6 ወሩ በሆም ኦፊስ ይመረመራሉ።

**ስለ የተበላሸ ነገር እንዴት ማሳወቅ እችላለሁ፧**
በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ ማንኛውም ችግር/ጉድለት ለመመዝገብ እና ለመጠገን እንዲቻቻል ወደ ማይግራንት ሄልፕ ሪፖርት መደረግ አለበት። የመኖሪያ ቤት አቅራቢዎች የተከሰተዉ ብልሽት በተወሰኑ የጊዜ ገደብ ዉስጥ ለመጠገን ይሰራሉ ("ጥገና እና ማስተካከያ" ን ይመልከቱ)። በአንድ ብልሽት/ጉድለት ከተጎዱ፡ ሪፖርት ለማድረግ መደበኛ ምርመራውን እስኪካሄድ መጠበቅ የለብዎትም።

**የመኖሪያ ቤት አቅርቦት**
የመኖሪያ ቤት አቅራቢው የመኖሪያ ቤቱን መግቢያ በር የቁልፍ ቅጂ ወይም ቤቱን የሚከፍት ቁልፍ ይይዛል፡ ይህም በአስተማማኝ ቦታ ይቀመጣል። ብዙውን ጊዜ የመኖሪያ ቤትዎን ለመጠገን እና ለመመርመር የሚመጣው እርስዎ ቤት ዉስጥ በሚኖሩበት ጊዜ ነው።

በአጭር ጊዜ ውስጥ መስራት ያለበት አስፈላጊ ስራ ካለ፡ የመኖሪያ ቤትዎ አቅራቢ መቼ ወደ መኖሪያ ቤትዎ እንደሚመጡ ለመንገር ያገኙዎታል። በዚያን ጊዜ በቤቱ ውስጥ መቆየት ካልቻሉ፡ የመኖሪያ ቤቱ አቅራቢ በራሱ ቁልፍ በመጠቀም ወደ ቤቱ መግባት ይችላል።

በመጀመሪያው መኖሪያ ቤት እንግዶች እንዲመጡ ይፈቀድላቸዋል፡ ነገር ግን እንግዶችዎ በፍጥነት ወደ ቤት እንዲገቡ እንዲያስችል የሚመጡበት ቀን እና ሰኣትን ለመኖሪያ ቤትዎ እንግዳ መቀበያ ሪሴፕሽኖች አስቀድመው መረጃ መስጠት አለብዎት። እንግዶች በቤቱ ውስጥ ለማደር እንደማይፈቀድላቸው ልብ ይበሉ።.

## ጥገና እና ማስተካከያ

የቤቶች አቅራቢዎች በጉዳዩ ዓይነት ላይ በመመርኮዝ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ማንኛውንም ብልሽት ለመጠገን ይሰራሉ። ከዚህ በታች ያለው ሰንጠረዥ የተለያዩ ብልሽቶችን፡ የምላሽ ጊዜዎችን እና አንዳንድ የብልሽት ምሳሌዎችን ያሳያል። ስለ የጥገና ምደባ እርግጠኛ ካልሆኑ ወይም ሪፖርት የተደረጉ ብልሽቶችን በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካልተጠገኑ  ለማይግራንት ሄልፕን ማሳወቅ አለብዎት።

## ተጨማሪ የመኖሪያ ቤት መረጃ

### የእሳት አደጋ ደህንነት

በመኖሪያ ቤት አቅራቢዎች የሚቀርቡ ሁሉም መኖሪያ ቤቶች የጭስ ማሳወቅያ ደወል ኣልርም ሊኖራቸው ይገባል። በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ እሳት ከተከሰተ፡ ጭሱ አላርሙን ያስነሳዋል እና በተከፍተኛ ድምጽ በተከታታይ 'ቢፐ' የሚል ድምጽ ያሰማል።

የእሳት አደጋ ሲያዩ እርስዎ እና ቤተሰብዎ ማድረግ ያለብዎት:

- በአቅራቢያዎ ያለውን የእሳት ማንቂያ ኣላርም ያብሩ።
- በቤቱ ውስጥ ያሉትን መመሪያዎች በመከተል በፍጥነት ከህንፃው ወጥተው ወደ ተመደበው መሰብሰቢያ ቦታ ይሂዱ።
- እሳቱን ለማጥፋት አለመሞከር
- የግል ንብረትዎን ለማውጣት ብለዉ እንዳይቆሙ
- ከህንፃው በቅርብ በሚገኘው ደህንነቱ የተጠበቀ መውጫ ይውጡ
- ለእሳት አደጋ መከላከያ እና ለህይወት ማዳን አገልግሎት በስልክ ቁጥር 999 ይደውሉ እና የመኖሪያ ቤትዎን አቅራቢ ያሳውቁ።

ህይወትን አደጋ ላይ ሊጥል ስለሚችል ባትሪውን ከጭስ ማንቂያ ኣላርም ኣያዉጡት ወይም አይቁረጡት። የእሳት ማንቂያው ችግር ካለዉ እባክዎን የሰራተኞችን አባል በተቻለ ፍጥነት ያሳውቁ። እንዲሁም በሚኖሩበት ቤት የኣደጋ ግዜ ማምለጫ መንገድ እንደሚያዉቋቸዉ ማረጋገጥ አለብዎት። እርግጠኛ ካልሆኑ የአገልግሎት አቅራቢውን ሰራተኛ ያነጋግሩ።.

በራስዎ ምግብ የሚያዘጋጁበት የመጀመሪያ የመኖሪያ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ፡ ቤቱ በሚመረመርበት ጊዜ በየወሩ የጭስ ማንቅያ አላርም ይሞከራል። አላርሙ በየጊዜው 'ቢፐ' የሚል ድምጽ ማሰማት ከጀመረ፡ ይህ ማለት ባትሪው መቀየር አለበት ማለት ነው። ባትሪውን ለመቀየር ማይግራንት ሄልፕ ያነጋግሩ።

### ንጽህና

መኖሪያ ቤቱ በንጹህ መንገድ መያዝ አስፈላጊ ነው፡ አንዳንድ የመጀምርያ የመኖሪያ ቤት ዓይነቶች (እንደ ሆቴሎች እና ሆስቴሎች) ለመኝታ ክፍሎች እና ለጋራ አካባቢዎች ሳምንታዊ የጽዳት አገልግሎቶች አሏቸው፡ ነገር ግን የመኖሪያ ቤቶቹ ንጹህ ካልሆኑ በቤትዎ ውስጥ የሰዎችን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል ተባይ ሊፈጥር ይችላል። በመኖርያ ቤታቹ ዉስጥ ያለዉን የጽዳት ደረጃ የመጠበቅ ሃላፊነት የእርሶ ነዉ።

የራስዎን ምግብ በሚያበስሉበት ቤት ወይም ሆስቴል ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ የመኖርያ ቤቱ አቅራቢ የጋራ ቦታዎችን በመደበኛነት የማጽዳት ኃላፊነት አለበት፡ ምንም እንኳን እርስዎ እና ሌሎች ነዋሪዎች እነዚህን አካባቢዎች መንከባከብ ቢኖርባቸውም። እንደ ብሌች፡ የመሬት ጽዳት (ፍሎር ክሊነር)፡ የማጠቢያ ፈሳሽ(ዎሺንግ አፕ ሊክዩድ)፡ መገልገያዎች ቦታዎች ማጽጃ(ቶፕ ክሊነር) እና የመሳሰሉት ለጋራ አካባቢዎች መሰረታዊ የጽዳት መገልገያዎችን ይሰጣል።

**ቆሻሻ መጣል (ምግብዎን በራስዎ በሚያዘጋጁበት መኖሪያ ቤት ውስጥ)**

ቆሻሻ በትክክለኛው የጠቅላላ ቆሻሻ መያዣ (ጄኔራል ዌስት) ወይም እንደገና ጥቅም ላይ በሚውለው መያዣ (ሪሳይክል) ውስጥ መጣል አለበት። የአካባቢው ካዉንስል እነዚህን ቆሻሻዎች በመደበኛ ቀናቶች ይወስዳል፡ ስለዚህ በትክክለኛው ቆሻሻ የሚወሰድበት ቀን ላይ ቆሻሻዎን እንዲወሰድ መውጣትዎን ያረጋግጡ።
በመንገድ ላይ ወይም በሌሎች የህዝብ ቦታዎች ላይ ቆሻሻ መጣል ሕገ-ወጥ ድርጊት ነው። ይህ ፍላይ-ቲፒንግ በመባል ይታወቃል። በፍላይ-ቲፒንግ ጥፋተኛ ሆነው ከተገኙ፡ ሊቀጡ ወይም ሊታሰሩ ይችላሉ።

**ጉዞ**

ሁሉም የሴክሽን 98 እና ሴክሽን 4 ድጋፍ የሚያገኙ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ትራንስፖርት ማዘጋጀት፡ የህዝብ ትራንስፖርት ትኬት በመስጠት ወይም በተወሰኑ ሁኔታዎች የጉዞ ትኬት ወጪን ለመሸፈን የአንድ ጊዜ የጉዞ ድጋፍ የማግኘት መብት አላቸው። ይህ የሚከተሉትን ጉዞዎች ሊያካትት ይችላል፡

- የልደት እና የሞት መዝገብ ቢሮ ለልጅ መውለድ ወይም ለቅርብ ሰው ሞት ለመመዝገብ።
- የሐኪም፡ የጥርስ ሐኪም፡ ወይም የሆስፒታል ቀጠሮ፡ እንዲሁም/ወይም
- ከወሊድ በፊት ወይም በኋላ የሚደረግ ቀጠሮ

በአጠቃላይ፡ የሴክሽን 95 ድጋፍ ከተሰጥዎት የሚሰጠውን የገንዘብ ድጋፍ በመጠቀም የራስዎን የጉዞ ወጪዎች እንዲሸፍኑ ይጠበቃል፡ ስለዚህ ተጨማሪ ድጋፍ አይሰጥም።

ሆኖም ግን፡ ከጓደኛ ወይም ከቤተሰብዎ ጋር መኖር ስለሚችሉ የጥገኝነት ጠያቂዎችን መኖሪያ ለመተው መምረጥ ይችላሉ። ሆም ኦፊስ አስፈላጊ የሆኑ ፍላጎቶችዎን ለመሸፈን የሚረዳዎትን የኑሮ ድጋፍ ካፀደቀ ከየጥገኝነት ጠያቂዎች መኖርያ ቤት ወደ ሊኖሩበት ለወሰኑ የጓደኛ ወይ ቤተሰብ አዲስ አድራሻ መጓዝ እና ማንኛውንም ምክንያታዊ የጉዞ ወጪዎች መሸፈን ሊያግዙት ይችላል። ለእንደዚህ ዓይነት እርዳታ ለማመልከት የኤ.ኤስ.ኤፍ2 ቅጽ መጠቀም ወይም በማይግራንት ሄልፕ አዲስ ሁኔታ የማሳወቅ ሂደት መጠቀም አለቦት እናም የጓደኛ ወይ ቤተሰብ የሆነ ከአዲሱ አድራሻዎ ጋር የሚደረግ ጉዞ ማስረጃ ማቅረብ አለብዎት።

ይህ ገንዘብ የሚሰጠው የጉዞ ዘዴዎ እና ወጪዎ ከሁኔታዎ አንጻር ምክንያታዊ ከሆነ ብቻ ነው። ይህ በአጠቃላይ ርካሽ የሚባለዉን የህዝብ ማመላለሻ አማራጭ በመጠቀም የጉዞ ሂደት መሆን አለበት።

**ፖስታ**

የእርስዎ ፖስታ የእርስዎ የግል ነው። የሌላ ሰው ፖስታ ውስጥ መግባት ወንጀል ነው። በመኖሪያ ቤትዎ ውስጥ የማይኖር ሰው ፖስታ ከመጣልዎት፡ ለሃውሲንክ ኦፊሰር እንዲያስረክቡ ይጠይቁ።
አብዛኛዎቹ የሆም ኦፊስ የሚመጣ ደብዳቤዎች በፖስታ የሚላኩ ይሆናሉ፡ ስለሆነም በሆቴሉ ዉስጥ የእንግዳ ተቀባይ ሪሴፕሽኖች በየጊዜው የርሶ ፓስጣ ወደ ሆቴሉ መጥቶ ከሆነ መጠየቅ ኣስፈላጊ ነዉ፡ ወይም ደሞ እራሱ የቻለ መኖርያ ቤት እየኖሩ ከሆነ በፖስታ ሳጥን ውስጥ ማግኘት ይችላሉ፡ እና ስለ ማንኛውም የአድራሻ ለውጥ ለሆም ኦፊስ ማሳወቅ አስፈላጊ ነው።

**የመኖሪያ ቤት መቀየር እና የመኖሪያ ቦታዎን ለመቀየር መጠየቅ**

ከጊዜ ወደ ጊዜ የመኖሪያ ቦታን ለመቀየር ሊጠየቁ ይችላሉ። ለምሳሌ፡ ወደ የኋለኛዉ ሲበተኑ የሚኖሩበት መኖርያ ቤት ሲዟዟሩ፡ የቤቱ ባለቤት ቤቱ እንዲመለስለት ከጠየቀ፡ በጤና እና ደህንነት ምክንያቶች ዙሪያ የሕግ ግዴታዎችን ማክበር ካለባቸዉ፡ የአገልግሎት ተጠቃሚ ልዩ ፍላጎቶችን ማሟላት ወይም ለመኖሪያ ቤቱ ከፍተኛ ጥገና ካስፈለገዉ። ሆም ኦፊስ እና የመኖሪያ ቤት አቅራቢዎ እርሶ ባሉበት ቦታ የሚያስፈልጉዎትን ሁሉንም አስፈላጊ ነገሮች እንደተሟላ ያረጋግጣሉ፡ ግን የመኖሪያ ቤት ያለ ምንም ምርጫ ነው የሚሰጠዉ፡ እናም ሁሌ ኣንድ ኣከባቢ ብቻ መቆየት የማይቻል ነው። ኣንተን ወዴ ሌላ ቦታ መቀየር ከፈለጉ ይህንን እንዳቀዱ የሚያረጋግጥ

ደብዳቤ ይልክልዎታል። ኢሜልዎ በፋይልዎ ውስጥ ከተመዘገበ ይህ ለእርስዎ በኢሜይል ይላካል፡ ወይ ደሞ በፖስታ ይላካል። እንደ አጠቃላይ ደንብ፡ የአገልግሎት አቅራቢው ሁኔታው ይህንን እንዲያደርጉ በሚያስችላቸዉ ሰአት ከ 5 ቀናት በፊት ስላቀዱት እርሶን ወደ ሌላ ቦታ የሚዟዟር እቅድ መረጃ ይሰጥዎታል። ሆኖም ግን ይህ በአጭር ጊዜ ውስጥ (ለምሳሌ የበኋላ ከመጀመርያ መኖርያ ቤት ወጥተዉ የሚመደቡበት ቤት ከተገኘሎት ወይም በአሁኑ መኖሪያዎ የጤና እና የዋስተና ችግር በሚኖርበት ሰአት) ኣስቀድመዉ የማሳወቅ ሂደት ማካሄድ እማይቻል ሊሆን ይችላል።

ምንም እንኳን አስቀድመው ወዴት እንደሚሄዱ ትክክለኛ አድራሻ ባይሰጡዎትም፡ ስለ አካባቢው (ለምሳሌ መንደር ወይም ከተማ) መረጃ ይሰጦታል፡ እና ወደዛን መኖርያ ቤት የሚወስዶት የትራንስፖርት አገልግሎት የሚዘጋጅ ይሆናል። መያዝ የሚፈቀድ ከፍተኛ የሻንጣዎች ብዛት በአንድ ሰው ሁለት ሻንጣዎች ነው፡ ከዚ ዉጪ የልጆች መጫወቻዎች እና ሌሎች ዕቃዎች፡ የህፃናት እንክብካቤ መገልገያዎች፡ የህክምና መሳሪያዎች፡ የልጆች ጋሪ ባግይ እና/ወይም ትራም እና አስፈላጊ ከሆነ የአካል ጉዳተኛነት ድጋፍን ነዉ የሚፈቀደዉ።

ሆኖም ግን፡ ሆም ኦፊስ በተወሰነ ቦታ እንዲመደቡ የሚጠይቁ ማናቸውንም ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት – እዚህ የመኖሪያ ቤት ምደባ መመሪያን ማግኘት ይችላሉ፡ በአሁኑ ጊዜ ያለዎት ወይም እንዲገቡበት የታሰበ ቤት በቂ እንዳልሆነ ከተሰማዎት ወይም ያሎት ግላዊ የሚያስፈልጋቹ ነገሮች እንደማያሟላ ከተሰማዎት፡ ይህንን የሚደግፍ ማስረጃ ወደ ማይግራንት ሄልፕ ያስገቡ። እነዉ ደሞ ይህ ማስረጃ ለሆም ኦፊስ ያካፍሉታል። ሆኖም ግን፡ ስምምነት ላይ የተደረሰባቸዉ ገደቦች ከሌሉ፡ የመኖሪያ ቤቱን አቅርቦቱን እንደሚቀበሉት ነዉ የሚጠበቀዉ (https://www.gov.uk/government/publications/asylum-accommodation-requests-policy)

## ክፍል 5 ገንዘብ እና የድጋፍ ክፍያ

የምግብ አቅርቦት ባለበት መኖሪያ ቤት ውስጥ ከሆኑ፡ በመኖሪያ ቤት አቅራቢዎ በማይሰጡበት ጊዜ እንደ ልብስ ያሉ አስፈላጊ የኑሮ ፍላጎቶችን ለመሸፈን ሳምንታዊ የገንዘብ ድጋፍ ማግኘት ይችላሉ።

ምግብዎን በራስዎ የሚያዘጋጁበት መኖሪያ ቤት ዉስጥ ከሆኑ እና የራስዎን ምግብ የሚያበስሉ ከሆነ፡ ለምግብዎ እና ለመጸዳጃ ቤት የሚያስፈልጉትን ተጨማሪ ወጪዎች ለመሸፈን የሚሰጦትን ሳምንታዊ የገንዘብ ድጋፍ መጠን ይጨምራል።

በጥገኝነት ማመልከቻዎ ላይ ውሳኔ በሚጠብቁበት ጊዜ ከጓደኛዎ ወይም ከቤተሰብዎ ጋር ለመኖር ከመረጡ፡ እንዲሁም አስፈላጊ የኑሮ ፍላጎቶችዎን ለመሸፈን ሳምንታዊ የገንዘብ ድጋፍ እንዲሰጡ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። የበለጠ ለማወቅ፣ እባክዎ የስደተኛ እገዛን ያነጋግሩ።

ለሴክሽን 95 ድጋፍ ተቀባይነት ካገኙ ወደ አድራሻዎ የአስፔን ካርድ ይላክሎታል። በሴክሽን 95 መሠረት ተቀባይነት እንዳገኘዎት የሚገልጽ ደብዳቤ ከተቀበሉ በኋላ ይህ ካድር ካልመጣሎት ለማይግራንት ሄልፕ ያነጋግሩ። ነገር ግን ካርድዎን ሲቀበሉ ለእርስዎ የሚገባዎት ድጋፍ ካርዱ ዉስጥ ገብቶ ዝግጁ ሆኖ ይጠብቆታል። ስለሚሰጥዎት የገንዘብ ድጋፍ ደረጃ ማንኛውም ጥያቄ ካለዎት ወይም የአስፐን ካርድ ከተሰጥዎት በኋላ ከጠፋቦት ማይግራንት ሄልፕ ያነጋግሩ። የአስፐን ካርድዎ ቺፐ-ኤንድ-ፒን (ካርዱ በማስገባት የፒን ቁጥሩን በመጻፍ) የሚጠቀም ሲሆን ከዚህ በታች እንደሚታየው ይመስላል።

**ስለ አስፐን ካርድዎ መረጃ**

ይህ የክሬዲት ካርድ አይደለም የባንክ ሂሳብም አይከፍትም። በካርድዎ ላይ ገንዘብ ማስገባት የሚችለው ሆም ኦፊስ ብቻ ነው፡ ስለዚህ ከሌሎች ክፍያዎች ለመቀበል ይህንን መጠቀም አይችሉም።

ሆም ኦፊስ እርሶን የሚገባዎት የገንዘብ ድጋፍ መጠን ያሳውቅዎታል፡ እናም በየሳምንቱ በካርድዎ ውስጥ ገንዘዉ ይገባሎታል። የሚሰጡት መጠን ከሳምንት እስከ ሳምንት የሚሸፍን ነዉ። በካርዱ ውስጥ ያለዉን ገንዘብ ብቻ ነዉ መጠቀም የሚችሉት። ነገሮችን ከመግዛትዎ በፊት በቂ ገንዘብ እንዳለዎት ማወቅ ያስፈልግዎታል፡ ካልሆነ ለመክፈል ሲሞክሩ እምቢ ሊል ይችላል፡ ካርዱ የፒን ቁጥር የተመደበለት ሰው ብቻ ነው ሊጠቀምበት የሚገባዉ፡ ይህም

ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ የመያዝ የርሶ ሃላፊነት ነው። የእርሶ ቤተሰብ ድጋፍ የሚሰጣቸዉ ከሆኑ፡ ዋናዉ ኣመልካች(ለድጋፍ ያመለከተ ሰዉ) ለቤተሰቡ የሚሆን ኣስፐን ካርድ ይይዛል።

ሆም ኦፊስ ማጭበርበርን ለመከላከል እና ደንበኞቻችንን ደህንነት ለመጠበቅ የካርዱን አጠቃቀም ሊመረምር ይችላል።በካርዱ ላይ ያለው የኤክስፓየር ቀን/ማብቂያ ቀን የድጋፍ ጊዜው የሚያበቃበት ቀን ነው ማለት አይደለም። ካርዱ ኤክስፓየር ከሆነ በኋላም የፋይናንስ ድጋፍ እየተቀበሉ ከሆነ ካርዱ ይታደስሎታል። ኮንታክትለስ ክፍያ(ካርዱን ሳያስነኩ ክፍያ መፈጸም)፡ በስልክ ወይም በኢንቴርኔት ክፍያዎችን ማድረግ ወይም ከዚህ ሀገር ውጭ ካርድዎን መጠቀም አይችሉም። ካርድዎ የተወሰኑ እቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ከመግዛት ሊከለክልዎ ይችላል። እባክዎን ተጨማሪ ወደ የጤና እንክብካቤ የሚሰጦት ለመሄድ የሚያስፈልጎት ተጨማሪ ክፍያ ካስፈለጎት ለማይግራንት ሄልፐን ያነጋግሩ።

**የአስፐን ካርድዎን ለሚከተሉት መጠቀም ይችላሉ፡**

- በአብዛኛዎቹ የማስተርካርድ ምልክት ያላቸው ሱቆች የችርቻሮ ክፍያ ለመክፈል፡ በካርዱ ላይ ያለው የገንዘብ መጠን ይወስናል።.
- የቀረው ቀሪ ሂሳብዎን በኤቲኤም ይመልከቱ፡ ይህም የገንዘብ ማሽን ተብሎም ይጠራል።
- ከጥሬ ገንዘብ ማሽን ጥሬ ገንዘብ ማውጣት፡ እስከ 200 ፓውንድ የሚደርስ ገንዘብ፡ ነገር ግን አንዳንድ የጥሬ ገንዘብ ማሽኖች ይህን ሲያደርጉ ክፍያ ስለሚጠይቁ ይጠንቀቁ።
- በማስተርካርድ የሚሳተፉ ሱቆች የሆነ ነገር ሲገዙ ገንዘብ መመለስ (ካሽ ባክ መቀበል)።

**ነገር ግን የጥገኝነት ጥያቄዎ ውድቅ ከተደረገ እና በሴክሽን 4 ድጋፍ ላይ ከሆኑ ከጥሬ ገንዘብ ማሽን ገንዘብ ማውጣት ወይም ከሱቆች ካሽባክ መውሰድ አይችሉም።**

የሚከተሉት ነገሮች ከተከሰቱ፡ ለማይግራንት ሄልፕ በስልክ ቁጥር **0808 8010 503** በተቻለ ፍጥነት ያግኟቸው።

- የሚጠብቁት የገንዘብ ክፍያ ሳይመጣ ሲቀር፡ ወይም የተሳሳተ የገንዘብ መጠን ሲመጣልዎ።
- ካርድዎ ከጠፋ፡ ከተበላሸ ወይም ከተሰረቀ (ይህ በመሰረዝ እና ሌላ ካርድ እንዲሰጠዎት)

## ተጨማሪ ክፍያ

**ለማንኛውም ተጨማሪ ክፍያ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ ብለው ካሰቡ፡ ለማይግራንት ሄልፕ በስልክ ቁጥር 0808 8010 503 ያነጋግሩ።** ከዚህ በታች ያለው መረጃ እርስዎ ብቁ ሊያደርግዎት ከሚችሉ ጉዳዮች ውስጥ አንዳንዶቹን ይገልጻል፡

**እርግዝና**

እርጉዝ ከሆኑ እና በኢሚግሬሽን እና ጥገኝነት ህግ 1999 ሴክሽን 4፡ 95 ወይም 98 መሰረት ድጋፍ የሚያገኙ ከሆነ፡ አዲስ ልጅ ከመውለድ ጋር የሚፈጠር ወጪዎች ለመርዳት ለኣንድ ግዜ ብቻ የሚከፈል የወሊድ ክፍያ ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

ይህንን ጥቅም ለመቀበል ልጅዎ ከመወለዱ ከ 8 ሳምንታት በፊት እና ከተወለደ በኋላ እስከ 6 ሳምንታት መካከል ባለዉ የግዜ በጽሑፍ ማመልከት አለብዎት። ልጅዎ ከመወለዱ በፊት ለማመልከት ልጁ ይወለዳል ተብሎ ለሚጠበቀው ቀን የሚያሳይ እንደ ኦሪጅናል ማትቢ1 (MATB1) ሰርተፊኬት ወይም ሌላ የእርግዝና የሕክምና ማረጋገጫ  ለማይግራንት ሄልፕ ማሳየት ያስፈልግዎታል። ልጅዎ ከዩኬ ውጭ ከተወለደ እና እድሜዉ ከ 3 ወር በታች ከሆነ ወይም በሌላ ልዩ ሁኔታዎች ውስጥ ማመልከት ይችላሉ። የልጅዎ እድሜ የሚያሳይ ታማኝ የሆነ ማስረጃ ማሳየት ኣለብሽ፡ ይህ እንደ የልጅዎ ዋነኛዉ ረጅም የምስክር ወረቀት ይሆናል።

በተጨማሪም በእርግዝናዎ ወቅት ተጨማሪ ሳምንታዊ የድጋፍ ክፍያ የመክፈል መብት ሊኖርዎት ይችላል፡ ይህ ደሞ ተጨማሪ የእርግዝና ክፍያ ተብሎ የሚታወቅ ሲሆን፡ እንዲሁም ተጨማሪ ኣስፈላጊዉን ምግብ ለመግዛት የሚሰጥ ነዉ። እርግዝና ክፍያ ህጻኑ ከመወለዱ በፊት ማነኛዉ ግዜ በ ማይግራንት ሄልፕ በኩል በጽሑፍ መጠየቅ

ይችላሉ። እንደ ኦርጅናል ማትቢ1 ሰርተፍኬት ወይም ከ ሚድዋይፍ የሚመጣ ደብዳቤ ወይም ከኣጠቃላይ ሃኪም ጂፒ የሚመጣ ደብዳቤ ያሉ እርግዝናውን የሚያረጋግጥ የህክምና ማስረጃ ማቅረብ ይኖርብዎታል።

ልጅዎ ከተወለደ በኋላ ከተለመደው ድጎማ በተጨማሪ ተጨማሪ ሳምንታዊ ድጎማ ማመልከት ይችላሉ፡ ይህም እስከ የመጀመርያ ኣመት ክርስትና ቀኑ ድረስ ነው፡ እና የኋለኛዉ ከተበተኑ በኋላ የሚገቡበት ቤትዎ ወይም ምግብ በራስዎ እያበሰሉ የሚኖሩበት መኖርያ ቤት ዉስጥ እየኖሩ ከሆነ ከ 1 እስከ 4 ዓመት ለሆኑ ማንኛውም ልጅ ልዩ ሳምንታዊ ድጎማ ማመልከት ይችላሉ። ይህንን የገንዘብ ድጋፍ ለመቀበል ዕድሜያቸውን ለማረጋገጥ ኦርጂናሉ ረጅም የልደት ሰርተፍኬት ከህክምና ማስረጃ ጋር ማቅረብ ይኖርብዎታል፡ ልጅዎ ከተወለደ በኋላ ደሞ በ6 ሳምንት ዉስጥ ይህንን ማድረግ ኣለቦት። በማይግራንት ሄልፕ በኩልም ማመልከት ኣለባችሁ።

ለእናቶች እና ለትንንሽ ልጆች ተጨማሪ ክፍያ ለማግኘት የሚከተለውን ይዚህ ይጎብኙ፡ (https://www.gov.uk/asylum-support/what-youll-get)

**ልዩ ሁኔታዎች**

በመደበኛ የድጋፍ መጠን ከሚሸፍነዉ በላይ ከፍተኛ ወጪ የሚፈጥር ልዩ ሁኔታ ካለዎት፡ ተጨማሪ ክፍያ ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ (ይህ **ሴክሽን 96** ክፍያዎችች በመባል የሚታወቅ ነዉ)። ለምሳሌ፡ ለሕክምና ቀጠሮዎች ረጅም ርቀት መጓዝ ካለብዎት (ይህ ከመጓዝዎ በፊት መጠየቅ አለበት) ወይም ልዩ አመጋገብ የሚጠይቅ የሕክምና ሁኔታ ካለዎት። ይህ ለማድረግ ማይግራንት ሄልፕ ጋር በመገናኘት ኤ.ኤስ.ኤፍ2 (ASF2) ይሞሉ - (https://www.gov.uk/government/publications/application-for-additional-asylum-support-form-asf2)

ከጓደኛዎ ወይም ከቤተሰብዎ ጋር መኖር ስለሚችሉ ከሆም ኦፊስ መኖርያ ቤት መውጣት ከፈለጉ እና በሴክሽን 95 ስር የፋይናንስ ድጋፍ ብቻ ካመለከቱ፡ ሆም ኦፊስ ምክንያታዊ ከሆነ እና በጣም ርካሽ የሆነውን የህዝብ ትራንስፖርት አማራጮችን (ካለ) የሚጠቀሙ ከሆነ ወደ አዲሱ የሚሄዱበት የጓደኛ ወይ ቤተሰብ መኖርያ አድራሻዎ የመጓጓዣ ወጪን ሊሸፍን ይችላል። ማይግራንት ሄልፕን በማነጋገር ይህንን ዓይነት እርዳታ ለማመልከት የሁኔታ ለዉጥ ማመልከቻ ቅጽ (ሲ.ኦ.ሲ/CoC) መሙላት ኣለባቹ፡ ከአዲሱ የሚኖሩበት የጓደኛ ወይ ቤተሰብ መኖርያ ቤት አድራሻ ጋር የሚያያዝ የጉዞ ወጪ ማስረጃ ማቅረብ አለብዎት። (https://www.gov.uk/government/publications/application-for-additional-asylum-support-form-asf2) (https://www.gov.uk/government/publications/notification-of-change-of-circumstances-form-mcc)

## ክፍል 6 የጥገኝነት ጥያቄዎ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ምን ማድረግ እንዳለብዎት

የጥገኝነት ጥያቄዎ (ማንኛውም ይግባኝ ጨምሮ) ውሳኔ ሲያገኙ፡ ብዙውን ጊዜ የሆም ኦፊስ ድጋፍ የማግኘት መብትዎ ይቋረጣል። ይህ ከሆነ፡ የገንዘብ ድጋፍዎ እንደሚቆም እና ከመኖሪያ ቤትዎ መውጣት እንዳለብዎት (ከመጀመሪያው ወይም ከመጨረሻው ከተበተኑ በኋላ የሚኖሩበት ቤት) ማሳወቂያ ይደርስዎታል።

ከዚህ በኋላ ምን ማድረግ እንዳለብዎ የጥገኝነት ጥያቄዎ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ውጤት በማግኘቱ ላይ የተመሰረተ ነው። ውሳኔው ሲሰጥ፡ ማይግራንት ሄልፕ በአጭር ጊዜ ውስጥ ያገኝዎታል እና በሚቀጥሉት እርምጃዎች ላይ ምክር ይሰጥዎታል። ለተጨማሪ ምክር የካውንስል የቤት ኣልባ ሆምለስ ቡድንን ማግኘት ይችላሉ።

የ ሊቭ ቱ ሪሜይን የመኖሪያ ፈቃድ ከተሰጠዎት(ኤል.ቲ.ኣር) ከመኖሪያ ቤቱ ለመውጣት ቢያንስ 28 ቀናት እና አሉታዊ ውሳኔ ከተሰጦት ከመኖርያ ቤቱ ለመውጣት 21 ቀናት ይኖራቸዋል። ከመኖሪያ ቤቱ ከመውጣታችሁ በፊት ሁሉም የግል ንብረቶችዎ እንደሰበሰቡ ያረጋግጡ እናም ቤቱ ንጹህ መሆኑን እና ማንኛውንም የእርሶ የግል ንብረት አለመተውዎን ያረጋግጡ። ማንኛውም ቤቱ ዉስጥ የተዉትን እቃ ከመጣሉ በፊት ለ28 ቀናት በማከማቻ ውስጥ ይቆያል።

### የተሳካ የጥገኝነት ጥያቄ

በዩኬ ውስጥ ለመቆየት ፈቃድ ከተሰጣችሁ - ወይ የረፊጂ ስታተስ፡ ወይም ኪስክረሽናሪ ሊቭ፡ ወይ ሁማኒተርያን ፕሮቴክሽን - ከተሰጦት ከዚያ ስራ መሥራት፡ ያሉትን የጥቅማ ጥቅም በነፊት ማመልከት እና ለግል መኖሪያ ቤት ማመልከት ይችላሉ (ለካዉንስል የቤቶች ድጋፍ ብቁ ሊሆኑ ቢችሉም) እና እንደ ሌሎች የዩናይትድ ኪንግደም ነዋሪዎች በተመሳሳይ እነኚህ እርዳታ ለመቀበል ብቁ ይሆናሉ። ኢ-ቪዛ ይሰጣችኋል። እናም ብቁ እንደሆኑ ለማሳየት ይህንን ኢቪዛ መጠቀም ይችላሉ።

የጥኝነት ጠያቂዎች ድጋፍ መብትዎ የጥገኝነት ጥያቄዎ ተቀባይነት እንዳገኘ የሚገልጽ ደብዳቤ ከተሰጦት ቀን ጀምሮ ከ28 ቀናት በኋላ ያበቃል። እያገኙት ያለዉን የጥኝነት ጠያቂዎች ድጋፍ የማቋረጥ ደብዳቤ (አሳይለም ሳፖርት ዲስኮንቲኔሽን ሌተር) ይሰጦታል። ይህም ድጋፉን የሚያበቃበትን ቀን የሚያሳይ ደብዳቤ ነዉ። ከጥኝነት ጠያቂዎች የሚሰጡት ድጋፍ ለመሸጋገር ግዜ ሊፈጅ ስለሚችል የውሳኔ ደብዳቤ እንደደረሶት ወዲያውኑ የወደፊት ዕቅዶችዎን ማዘጋጀት መጀመርዎ አስፈላጊ ነው። ሆም ኦፊስ ድጋፉን ከሚያበቃበት ቀን የበለጠ ጊዜዉን ሊያራዝምሎት ኣይችልም።

ለሁሉም ግለሰቦች በማይግራንት ሄልፕ ወይም በአጋር ድርጅቶች በኩል ወደፊት የሜሄድ ድጋፍ (ሙቭ ኦን ሰርቪስ) እንሰጣለን። ማይግራንት ሄልፕ በታላቋ ብሪታንያ ውስጥ እንዲዋሃዱ ለመርዳት የተዘጋጀ ምክር ይሰጥዎታል።

መታወቂያ ኣይዲ ከሌለዎት ሆም ኦፊስ የ ዩኬቪአይ UKVI መለያ ይከፍትሎታል፡ ይህም ወደ ኢቪዛዎ እንዲገቡ እና ስለ ኢሚግሬሽን አገልግሎቶቻቸው መረጃን በ "እይታ እና ማረጋገጫ" (view and prove) አገልግሎት በመጠቀም እንዲያጋሩ ያስችልዎታል። ለምሳሌ ቤት በሚከራዩበት ሰኣት ቤት የመከራየት መብት እንዳለዎት ለማረጋገጥ። ይህ መለያ ኣካዉንት አዎንታዊ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ 14 ቀናት ውስጥ ለእርስዎ ይከፈታል።

ከትዉልድ ቀን ጋር በመጠቀም ወደ ኢ-ቪዛዎን ለመግባት ሊጠቀሙበት የሚችሉት ዩኬቪአይ ካስተመር ናምበር የሚባል አዲስ የእውቂያ ቁጥር ይሰጥዎታል። እንዲሁም ወደ ኣካዉንቶ ለመግባት ወደ ኢሜልዎ ወይም ስልክዎ መግባት ያስፈልግዎታል። ሕጋዊ ተወካይዎ ወይም ኃላፊነት ያለው ከኣስራ ስምንት በላይ እድሜ ያለዉ ሰውዎ ይህንን የኖቲፊኬሽን መረጃ በእርስዎ ምትክ ሊቀበል ይችላል፡ ሆኖም ግን ይህ በኦንላይን ሪካቨሪ ሂደት(ድጋሜ ማግኘት) በመጠቀም ሊፈታ ይችላል፡ ወይም ወደ ዩኬ ቪዛ ማዕከል (ዩኬቪአይ ሪዞልሽን ሰንተር) መደወል ወይም ዩኬ ቪዛ ኤንድ ኢሚግሬሽን መ/ተቀም ያስፈልጎታል። ኢቪዛዎ ማዘጋጀት ወይም ወደ አካዉንቶ መግባት ላይ ችግር ካጋጠሞት በማይግራንት ሄልፕ በኩል፡ ኣድቫይስ ኤን.አይ፡ ሲቲዝን ኣድቫይስ ስኮትላንድ፡ ዌልሽ ረፊጂ ስኮትላንድ ድጋፍ ማግኘት ይችላሉ። ሙሉ ዝርዝር መረጃ እዚህ ማግኘት ይችላሉ። GOV.UK. ([https://www.gov.uk/government/publications/evisa-community-support-for-vulnerable-people](https://www.gov.uk/government/publications/evisa-community-support-for-vulnerable-people))

የጥኝነት ድጋፍ ማቋረጥ ደብዳቤ (አሳይለም ሳፖርት ዲስኮንቲኔሽን ሌተር) ድጋፍ የሚቋረጥበትን ቀን ያካትታል፡ እንዲሁም የዩኬቪአይ መለያ ኣካዉንት ዝርዝር ቅጂን ያካትታል።

የ ዩኬቪአይ ኣካውንት ዝርዝሮችዎ ወይም የጥገኝነት ድጋፍ የማቋረጥ ደብዳቤዎ መቼ እንደተሰጦት ምንም ይሁን ምን፡ በቂ የሽግግር ጊዜ እንዲኖርዎት ከጥኝነት ድጋፍ ለመሸጋገር እቅድ ማውጣት መጀመር አስፈላጊ ነው። የ ዩኬቪአይ መለያ/ኢቪዛ ዝርዝሮችዎን ከመቀበሉልዎ በፊት አንዳንድ አስፈላጊ አገልግሎቶችን ማግኘት ይችላሉ እና የውሳኔ ደብዳቤው ከተሰጦት በኋላ በቤቶች፡ የዩኒቨርሳል ክሬዲት ማመልከቻ መክፈት እና የባንክ ሂሳብ መክፈት የመሳሰሉ ማደረግ ያለባቸዉ አስፈላጊ እርምጃዎች በግልጽ ያስቀምጣል።

የጥኝነት ማመልከቻ ካርድ (የአሳይለም ሪጂስትሬሽን ካርድ ኤ.አር.ሲ) ከጥገኝነት ጥያቄዎ ውሳኔ ጋር በመጠቀም የዩኒቨርሲቲ ክሬዲት ማመልከቻ መጀመር ይችላሉ።

የጥገኝነት ወደፊት የመሄድ ግኑኝነት መኮንን (ኤ.ኤም.ኤል.ኦ) በአንዳንድ የመጠለያ ቦታዎች ድጋፍ ይሰጣሉ። በመኖሪያ ቤትዎ ውስጥ ኤ.ኤም.ኤል.ኦ ካሉ ቀጠሮ ሊሰጡዎት ይችላሉ።

- ኤ.ኤም.ኤል.ኦ በሆቴሎች ወይም በሌሎች የመኖሪያ ቤቶች ውስጥ ለተጠቃሚዎች አገልግሎት ይሰጣል፡ እና አንዳንድ ጊዜ በስልክ ድጋፍ ይሰጣል።
- ኤ.ኤም.ኤል.ኦ በቅርቡ የመኖሪያ ፈቃድ የተሰጣቸው ሰዎች ከጥገኝነት ጠያቂዎች መኖሪያ ቤት እንዲወጡ እና በሕይወታቸው ቀጣይ ደረጃ ላይ ለሚደግፏቸው አገልግሎቶች በመምራት ይረዳቸዋል። እነሱ ከእርስዎ ጋር ስለ የሙቭ ኦን ዕቅዶች ወደፊት ለመሄድ ይወያያሉ እና ወደ ሊረዱዎት ለሚችሉ አገልግሎቶች ይመራሉ። ለምሳሌ የጎደሉ ሰነዶች ካሉ እነዚህን በሚሟላት ጉዳዮች በተቻለ ፍጥነት ለመፍታት ኤኤምኤልኦ ያፋጥኑታል።
- እንደ ጥገኝነት ውሳኔ ደብዳቤ፡ የ ኢቪዛ ኣካዉንት መለያዎች ዝርዝር እና የጥገኝነት ድጋፍ ማቆም ደብዳቤ ያሉ ሁሉም ኣስፈላጊ የሆኑት ሰነዶች እንዳለዎት ያረጋግጣል። ኤ.ኤም.ኤል.ኦ እንዲሁ እንደ ዩኒቨርሳል ክሬዲት ያሉ የዩኬ ጥቅሞችን በነፊት እንዲያገኙ ይደግፍዎታል።
- ኤ.ኤም.ኤል.ኦ ስለ መኖሪያ ቤት ምክር አይሰጡዎትም ወይም መኖሪያ ቤት አያቀርብም። የእነሱ ሚና ድጋፍ እንዳያገኙ ሊያግድዎት የሚችሉ መሰናክሎችን ማስወገድ እና ወደ ትክክለኛው አገልግሎት መምራት እንጂ በቀጥታ መኖሪያ ቤት ማቅረብ አይደለም።
- ኤ.ኤም.ኤል.ኦ ያለምንም ችግር ለመቀጠል የሚያስፈልጉዎትን ሰነዶች እና መመሪያዎች እንዳለዎት ያረጋግጣል።

### *ሥራ መፈለግ ወይም ጥቅማጥቅሞችን መጠየቅ*

*ሥራ መፈለግ* እና/ወይም ጥቅማጥቅም በነፊት መጠየቅ ያስፈልግዎታል። ጆብሰንተር ፕላስ እነዚህን ጉዳዮች የሚያስተናግድ የመንግስት መሥሪያ ቤት ነው። ማይግራንት ሄልፕ በዚህ ላይ ሊረዳዎት ይችላል፡ እና ከጆብሰንተር ፕላስ ጋር የመጀመሪያ ቀጠሮዎን ለመያዝ ይረዳዎታል። ይህንን በተቻለ ፍጥነት ማድረግ አስፈላጊ ነው።

### *አማራጭ መኖሪያ ቤት ማግኘት*

የራስዎን ማረፊያ ማግኘት ይኖርብዎታል። ይህ የኪራይ መኖርያ ቤት፡ ስራ እየሰሩ እዛዉ የሚኖሩበት ቤት፡ ሆስቴል፡ ፍላት ቤት ወይም እራስዎን ከሚያገኟቸው ሌላ ሰው ጋር በጋራ የሚኖሩበት ሃዉስ ሼር ሊሆን ይችላል። እንደ ማይግራንት ሄልፕ፡ የካዉንስል የመኖሪያ ቤት ክፍል ምክር እና እርዳታ ሊሰጥዎ ይችላል። ሆኖም ግን የራስዎን የግል ማረፊያ ማግኘት ያስፈልግዎታል፡ እና ካዉንስሉ እንደ ለከፍተኛ አደጋ ተጋላጭ የሆኑ ወይም ልጅ ካሎት የመሳሰሉ ልዩ ሁኔታዎች ካሉዎት ብቻ በካዉንስሉ የቤት ኣቅርቦት እንደሚጠቀሙ ልብ ይበሉ።

### የባንክ ሂሳብ መክፈት

ማንኛውንም የበኔፊት ጥቅማጥቅም ክፍያ ለማግኘት እና ኪራይ ካለብዎት የቤት ኪራይዎን ለመክፈል የባንክ ሂሳብ መክፈት ያስፈልግዎታል (እስካሁን ያልከፈቱ ከሆነ)። የተለያዩ ባንኮች ሂሳብ ለመክፈት የተለያዩ መረጃዎችን ይጠይቃሉ፡ ነገር ግን ሁሉም እንደ ቪዛ ያሉ የመለያ መረጃዎን ማየት ይፈልጋሉ።

## *ተቀባይነት ያላገኘ የጥገኝነት ጥያቄ*

በቤተሰብዎ ውስጥ ልጆች ከሌሉዎት የጥገኝነት ድጋፍ መብትዎ ከ 21 ቀናት በኋላ ይቆማል። ከመኖሪያዎ የሚለቁበትን ቀን የሚያመለክት ደብዳቤ ይሰጥዎታል። ከዩኬ ለመውጣት እርምጃዎችን የሚወስዱ ከሆነ ግን በ21 ቀናት ውስጥ ለመውጣት የማይችሉ እንደሆነ ካሙኑ ተጨማሪ ድጋፍ እንዴት እንደሚጠይቁ መረጃ ይሰጥዎታል። ይህ ዓይነቱ ድጋፍ 'ሴክሽን 4 ድጋፍ' በመባልም ይታወቃል እናም በሌላ ኣንዳንድ ሁኔታዎችም ሊኖር ይችላል፡ ይህ ደሞ በሚደርሶት ደብዳቤ ላይ ይገለጻል። ስለ የሴክሽን 4 ድጋፍ በተመለከተም ከማይግራንት ሄልፕ ምክር ማግኘት ይችላሉ።

የጥገኝነት ጥያቄዎ ወይም ይግባኝ ሂደት ተቀባይነት ሳያገኝ በቀረበት ግዜ ጊዜ በቤተሰብዎ ውስጥ ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ካሉ፡ የጥገኝነት ጠያቂዎች ድጋፍ ወዲያውኑ አይቋረጥም።

የጥገኝነት ማመልከቻዎ (ማንኛውንም ይግባኝ ጨምሮ) ውድቅ ከተደረገ፡ ከዩናይትድ ኪንግደም ለመውጣት ዝግጅቶችን ማድረግ ይጠበቅብዎታል። ሆም ኦፊስ ማንኛውንም አስፈላጊ ዝግጅት እንዲያደርጉ የሚያስችልዎ በበጎ ፈቃደኝነት የመመለስ አገልግሎት ይሰጣል። በዚህ ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት በበጎ ፈቃደኝነት የመመለስ አገልግሎት ሊጎበኙ ወይም ሊደውሉ ይችላሉ: **0300 004 0202**. ([http://www.gov.uk/return-home-voluntarily](http://www.gov.uk/return-home-voluntarily))

ውሳኔዎ ከተቀበሉ በኋላ በአጭር ጊዜ ውስጥ ማይግራንት ሄልፕ ያገኝዎታል እና ስለሚቀጥሉት እርምጃዎች ምክር ይሰጥዎታል፡ ይህም በበጎ ፈቃደኝነት የመመለስ አገልግሎት መረጃ እና ጥቅሞችን ያካትታል።

**ስለ ጥገኝነት ሂደት የበለጠ መረጃ ከፈለጉ፡ በታላቋ ብሪታንያ ውስጥ ባሉበት ሰአት ለእርሶ ስለሚገኙት የድጋፍ አገልግሎቶች ወይም ስለ መብቶችዎ እና ግዴታዎችዎ መረጃ ከፈለጉ እዚህ ማግኘት ይችላሉ፡**
([https://www.gov.uk/government/publications/information-leaflet-for-asylum-applications/information-booklet-about-your-asylum-application](https://www.gov.uk/government/publications/information-leaflet-for-asylum-applications/information-booklet-about-your-asylum-application))

## ክፍል 7 አስፈላጊ መገናኛዎች

**የአስቸኳይ ጊዜ/የአደጋ ጊዜ የኤመርጀንሲ መገናኛዎች፡:**
የአስቸኳይ ጊዜ የኤመርጀንሲ አገልግሎት (የእሳት አደጋ መከላከያ / ፖሊስ / አምቡላንስ)፡: **999**
አስቸኳይ ያልሆነ ፖሊስ: **101**
አስቸኳይ ያልሆነ ኤን ኤች ኤስ: **111**

**ብሄራዊ የጋዝ መስመር:**
ኢንግላንድ፡ ስኮትላንድ እና ዌልስ: **0800 111 999**
ኖርዘርን አየርላንድ: **0800 002 001**

**ማይግራንት ሄልፕ:**
**ዌብቻት** በሚግራንት ሄልፕ ዌብ ቻት (URL: https://www.timeforstorm.com/CustomChat/MigrantHelp/1/)
በዌብሳይት ላይ ያለዎትን **ጉዳይ ያቅርቡ:** (URL: https://selfserve.migranthelpuk.org/submit-issue/) (https://selfserve.migranthelpuk.org/submit-issue/)
**ነፃ የእገዛ መስመር ቁጥር** 0808 8010503.
(http://www.migranthelpuk.org)

**ሆም ኦፊስ:**
ስለ ጥገኝነት ማመልከት እና የጥገኝነት ድጋፍ መረጃ:
(http://www.gov.uk/browse/visas-immigration/asylum)

**የጥገኝነት ድጋፍ ይግባኝ:**
(http://www.gov.uk/courts-tribunals/first-tier-tribunal-asylum-support)

**ህጋዊ አማካሪ ለማግኘት:**
(http://www.gov.uk/find-a-legal-adviser)

**በበጎ ፈቃደኝነት የመመለስ አገልግሎት:**
ዊንሳይት: (http://www.gov.uk/return-home-voluntarily)
ስልክ: **0300 004 0202**

**የበጎ አድራጎት ድርጅቶች፡:**
ረፊጂ ኣክሽን: (http://www.refugee-action.org.uk/)
ረፊጂ ካዉንስል: (http://www.refugeecouncil.org.uk/)
አሳይለም ሳፖርት አፒል ፕሮጀክት (የድጋፍ ጥገኝነት ፕሮጀክት ይግባኝ): (http://www.asaproject.org/)
ቻይልድ ላይን (ከ18 ዓመት በታች ለሆኑ ነፃ፡ ሚስጥራዊ እና የምክር ድጋፍ ይሰጣል) ነፃ መስመር: 0800 1111 (https://www.childline.org.uk/)

© የቅጂ መብት የተጠበቀ ክራውን 2022

ይህ ጽሑፍ በሌላ መንገድ ካልተገለጸ በስተቀር በክፍት መንግስት ፈቃድ ስምምነት v3.0 መሰረት ፈቃድ ተሰጥቶታል። ይህንን ፈቃድ ለማየት (http://nationalarchives.gov.uk/doc/open-government-licence/version/3/)

ማንኛውም የሶስተኛ ወገን የቅጂ መብት መረጃ ካስተዋልን ከሚመለከታቸው ባለቤቶች የቅጂ መብት ፈቃድ ማግኘት ያስፈልግዎታል።

ይህ ጽሑፍ በ [ወይም በሌላ ዌብ/ኢንትራኔት አድራሻ] ላይ ይገኛል (http://www.gov.uk/government/publications)

ይህንን ጽሑፍ በተመለከተ ማንኛውም ጥያቄ ካለዎት እባክዎ በሚከተለው አድራሻ [insert contact details] ይላኩልን።